

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በግብርና ሚኒስቴር የእጽዋት ፀረ-ተባይ ኬሚካል ምዝገባ፣ አጠባበቅ እና አወጋገድ ሥርዓትን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ታህሣሥ 2003 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# ማውጫ


መግቢያ ........ 1
የሚኒስቴር መ/ቤቱ ዓለማ፣ ሥልጣንና ተግባር የግብርና ሚኒስቴር አጠቃላይ ዓላማዎች ........ 3
የሚኒስቴር መ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር ........ 4
የእንስሳትና ዕጽዋት ጤናና ጥራት ቁጥጥርና ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት ዓላማዎች ........ 5
የመ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅርና የሠው ኃይል ........ 5
የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ ........ 5
የኦዲቱ ዓላማ፤ ........ 6
ኦዲት ወሰንና ዘዴ ........ 6
የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ........ 7
የመመዘኛ መስፈርቶች /Evaluative Criteria/ ........ 8
የፀረ-ተባይ ምዝገባ የሥራ ሂደት መግለጫ ........ 9
የብቃት ኢንስፔክሽን የሥራ ሂደት መግለጫ ........ 14
ክፍል ሁለት ........ 17
ግኝቶች ........ 17
የፀረ-ተባይ መጋዘኖች አገነባብ ደረጃውን የጠበቀ መሆኑን በተመለከተ፣ ........ 17
የፀረ-ተባይ መጋዘኖች ከሠዎችና ከእንስሳት መኖሪያ አካባቢ ርቀው መሠራታቸውን በተመለከተ፣ ........ 20
የፀረ-ተባይ ኬሚካል መከላከያ ቁሳቁስ ለሠራተኞች የተሟላ መሆኑን በተመለከተ፣ ........ 23
የፀረ-ተባይ ኬሚካል መያዣዎች ለአጠቃቀም አመቺ መሆናቸውን በተመለከተ፣ ........ 25
የፀረ-ተባይ ኬሚካል ባህሪ የሚገልጽ መለያ (labeling) ተሟልቶ የማይለጠፍ መሆኑን በተመለከተ፣ ........ 25
ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ምዝገባን በተመለከተ፣ ........ 26
የፀረ-ተባይ የፍቱንነት ሙከራ ሪፖርቶች (Efficacy test) ወጥነት ያላቸው መሆኑን በተመለከተ፣ ........ 27
የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ናሙና ለምዝገባ በሚመጡበት እና ወደ ሀገር ውስጥ በብዛት (Bulk) በሚገቡበት ወቅት ስለትክክለኛነታቸው የላብራቶሪ ፍተሻ መከናወኑን በተመለከተ፣ ........ 27
የፀረ-ተባይ ኬሚካል መያዣዎች ዳግም ለሌላ ሥራ ጥቅም ላይ እንዳይውሉ ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን በተመለከተ ........ 28
የጤና ጥበቃ ሚኒሰቴር ተወካይ በፀረ-ተባይ አማካሪ ቦርድ ውስጥ መሳተፉን በተመለከተ፣ ........ 29
የፀረ-ተባይ አማካሪ ቦርድ የመግባቢያ ሠነድ መኖሩን በተመለከተ፣ ........ 30
የተቀናጀ የተባይ መከላከለያ (Integrated Pest Management) በአገር አቀፍ ደረጃ ተጠናክሮ መከናወኑን በተመለከተ፣ ........ 30
ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ የፀረ-ተባይ ፍላጐት ዳሰሳ ጥናት የሚያከናወን መሆኑን እና ግኘው በዚሁ መሠረት የሚፈፀም መሆኑን በተመለከተ ........ 32
የፀረ-ተባይ ኬሚካል አጠቃላይ መረጃዎችን ለአጠቃቀም በሚያመች መልኩ በዳታ ቤዝ ሥርዓት መያዙን በተመለከተ ........ 32
ጥቅም ላይ እንዲውሉ የተመዘገቡና የታገዱ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ለህብረተሰቡ በድረ-ገጽና በህትመት ማሳወቅን በተመለከተ ........ 33
የፀረ-ተባይ ኬሚካል አጠቃቀምና የግብይት ሥርዓት ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር የተጠናከረ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፣ ........ 34
ተመዝግበው ጥቅም ላይ የዋሉ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ውጤታማነታቸው የሚገመገም መሆኑን በተመለከተ፣ ........ 34

ለሰብልና ለእጽዋት አገልግሎት ላይ መዋል የማይገባቸው አደገኛ ኬሚካሎች በህገ ወጥ መንገድ ጥቅም ላይ እንዳይውሉ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ተገቢው ቁጥጥር መደረጉን በተመለከተ ..... 35
ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ህገ-ወጥ የፀረ-ተባይ ግብይትን ማስቆምን በተመለከተ፣..... 37
ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን አስመልክቶ ግንዛቤን የሚያሳድጉ በራሪ ጽሁፎችና የመወያያ መድረኮች ለክልሎችና ለአስመጪዎች በየወቅቱ መዘጋጀቱን በተመለከተ፣..... 41
ጊዜያቸው ያለፈባቸው (Obsolete) ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ጥቅም ከሚሰጡ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ተለይተው መቀመጣቸውን በተመለከተ..... 41
ለክልል የግብርና ባለሙያዎች ፀረ-ተባይን አስመልክቶ በቂ የግንዛቤ ማስጨበጫመሰጠቱን በተመለከተ፣..... 44
በፀረ-ተባይ ኬሚካል ማከማቻ መጋዘኖች ውስጥ ሌሎች ቁሳቁሶች የማይከማቹ መሆኑን በተመለከተ፣..... 46
ጊዜ ያለፈባቸው ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች እና በፀረ-ተባይ ኬሚካል የተበከሉ ቁሣቁሶች ለሰውና ለአካባቢ ጉዳት በማያደርስ መልኩ መጠበቃቸውን በተመለከተ፣..... 50
ጊዜ ያለፈባቸውን የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ለማሰባሰብ፣ ለማጓጓዝና ለማስወገድ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሠራ መሆኑን በተመለከተ፣..... 53
ጊዜያቸው ያለፈባቸው ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ለመከላከልና ለማስወገድ በሁለተኛው ዙር በዕቅድ የተያዘው ገንዘብ ሥራ ላይ መዋሉን በተመለከተ፣..... 54
**ክፍል ሦስት** ..... 55
**መደምደሚያ** ..... 55
**ክፍል አራት** ..... 59
**የማሻሻያ ሐሣቦች** ..... 59

**አባሪ**
**የመመዘኛ መስፈርቶች**

# መግቢያ

1. የአሁኑ ግብርና ሚኒስቴር እንደተቋም የተመሰረተው በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግስት የእርሻና የመሥሪያ ቤት ሚኒስቴር በሚል መጠሪያ በ1900 ዓ.ም ነው፡፡ ይህም ግብርና እንደተቋም ከተቋቋመ ከአንድ መቶ አመታት በላይ ያስቆጠረ መሆኑን ያሳያል፡፡ የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ያስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በመወጣው አዋጅ ቁጥር 4/1987 እንደገና ተቋቋመ፣ በድጋሚ የመንግሥት የአስፈፃሚ አካላትን አደረጃጀት ለማሻሻል ባወጣው አዋጅ ቁጥር 380/96 መሠረት ቀደም ሲል ራሳቸውን ችለው ይንቀሳቀሱ የነበሩ የግብርና ሚኒስቴር እና የገጠር ልማት ሚኒስቴር መ/ቤቶች በአንድ ላይ ተዋህደው ንዲደራጁ በማድረግ ንዲቋቋም የተደረገ ቢሆንም አሁን በሥራ ላይ የሚገኘው የግብርና ሚኒስቴር በ2003 ዓ.ም ያስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 ተሻሽሎ ተቋቁሟል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሕብረተሰቡን ከድህነት ማላቀቅ የሚያስችል የላቀ ቴክኖሎጂ የሚጠቀምና ከፍተኛ የምርታማነት ደረጃ ላይ የደረሰ ዘመናዊ የግብርና ሥርዓት መፍጠር የሚል ተልዕኮ ይዞ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡
2. የግብርና ሚኒስቴር የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ አድርጎ እየተንቀሳቀሰ ሲሆን በበፊቱ የሰብል ጥበቃ መምሪያ የነበረውንና በሥሩም የፀረ-ተባይ ምዝገባና ቁጥጥር ቡድን፣ የሰብል ጥበቃ ላብራቶሪና፣ ኳራንቲን ቁጥጥር ቡድን እና ሰብል ጥበቃ ቡድን ያካተተ የነበረው መምሪያ መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ (BPR) ተግባራዊ ከተደረገ በኋላ የእንስሳትና ዕጽዋት ጤናና ጥራት ቁጥጥርና ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት የሚል ስያሜ ተሰጥቶት እንደ አዲስ ተዋቅሯል፡፡
3. የእንስሳትና ዕጽዋት ጤናና ጥራት ቁጥጥርና ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት በሃገሪቱ ውስጥ በጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ የእጽዋት፣ የእንስሳት መድሐኒትና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ይመዘግባል ይቆጣጠራል፡፡ ዳይሬክቶሬቱም የሀገሪቱን የግብርና ሀብት ጤናና ጥራት በመጠበቅ እንዲሁም በእንስሳትና እጽዋት በተባይና በሽታ ምክንያት የሚከሰተውን የዜጐች ጤና ስጋት በመቀነስ የአለም አቀፍ የንግድ ስምምነቶች መከበራቸውን ማረጋገጥ፣ ከሀገር የሚወጡ ወደ ሀገር የሚገቡ የግብርና ምርቶችና ውጤቶችን ጥራትና ደህንነት በማረጋገጥ የደንበኛን ፍላጐት ማርካት እና አደገኛ መጤ የነፍሳት ተባይ፣ መጤ አረም፣ ድንበር ዘለል በሽታዎችንና ነፍሳት ተባዮችን በመገደብና በመቆጣጠር የግብርናና ተፈጥሮ ሀብትን መጠበቅ የእንስሳትና ዕጽዋት ጤናና ጥራትን በመቆጣጠር፣ የበሽታና ተባይ ቅኝት

በማካሄድ፣ የግብአት ጥራት ቁጥጥር አገልግሎትን አሰራር በማቀላጠፍና ሽፋኑን በማሳደግ የእንስሳትና እንስሳት ተዋጽኦዎች እንዲሁም የዕጽዋትና ዕጽዋት ውጤቶችን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ማሳደግ የሚል ራዕይና ዓላማ ይዞ የተዋቀረ ዳይሬክቶሬት ነው፡፡

4. ፀረ-ተባይ ኬሚካል ወደ አገራችን ውስጥ ከመቼ ጀምሮ መግባት እንደጀመረ በትክክል ለማወቅ ባይቻልም የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በ2004 እ.ኤ.አ ፀረ-ተባይ በአካባቢ ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት አስመልክቶ ባደረገው ጥናት ላይ እንደተገለፀው ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ወደ አገር ውስጥ መግባት እና ጥቅም ላይ መዋል የጀመሩት ከ1960ዎቹ ጀምሮ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ይህም ጥናት የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች በአማካኝ በየአመቱ ከ3000 ቶን በላይ ወደ አገራችን እንደሚገቡ ይጠቁማል፡፡ ለፀረ-ተባይ ኬሚካል ግዥም በአማካኝ በአመት 20 ሚሊየን የአሜሪካ ዶላር ወጪ እንደሚደረግም ያመለክታል፡፡ በአሁኑ ወቅት በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ፈቃድ ተሰጥቷቸው ያስገቡ ፀረ-ተባይ ኬሚካል አስመጪ ድርጅቶች መረጃ እንደሚያሳየው በአመት ከ3681 ቶን በላይ ፀረ-ተባይ ኬሚካል በ37 የፀረ-ተባይ አስመጪ ድርጅቶች እንደሚገባ ለማወቅ ተችሏል፡፡
5. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለረጅም ጊዜያት በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ተከማችተው የነበሩትን ጊዜያቸው ያለፈባቸውን የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ለማስወገድ ሶስት የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ ከ1992 ዓ.ም ጀምሮ እስካሁን ወደ 2200 ቶን የሚጠጋ ጊዜያቸው ያለፈባቸው ኬሚካሎችን እንዲወገዱ አድርጓል፡፡
6. በኢትዮጵያ ጊዜያቸው ያለፈባቸውን የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን የመከላከል እና የማስወገድ የመጀመሪያ ዙር ፕሮጀክት እ.ኤ.አ በ2000 ተጀምሮ እ.ኤ.አ በ2002 ተጠናቋል፡፡ በዚህም ፕሮጀክት ፀረ-ተባይን የሚመለከቱ የተለያዩ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡ የሀገሪቱን የላብራቶሪ ደረጃ በማሻሻል ጊዜያቸው ያለፈባቸውን ፀረ-ተባዮች ወደ ተመረጡ ማዕከላዊ ቦታዎች ተሰባስበዋል፡፡
7. የመጀመሪያው ዙር ፕሮጀክት ከለጋሽ ሀገሮች ማለትም ከአሜሪካ፣ ከኔዘርላንድና ከስዊድን በተገኘ 4,435,770 ዶላር (አራት ሚሊየን አራት መቶ ሠላሳ አምስት ሺህ ሰባት መቶ ሰባ ዶላር) እና ከኢትዮጵያ መንግስት በተገኘ 210,790 ዶላር (ሁለት መቶ አስር ሺህ ሰባት መቶ ዘጠና ዶላር) የተከናወነ ነው፡፡ በፕሮጀክቱ በቆጠራ የተገኘው የፀረ-ተባይ ኬሚካል መጠን 2900 ቶን ቢሆንም ከዚህ ውሰጥ 400 ቶን የሚሆነው ጥቅም የሚሰጥ መሆኑ በላብራቶሪ ፍተሻ በመረጋገጡ 2500 ቶን የሚሆነው እንዲወገድ ተወስኗል፡፡ ሆኖም

ከለጋሾች የተገኘው ገንዘብ በቂ ስላልነበር በመጀመሪያው ዙር ፕሮጀክት 1508 ቶን እንዲወገድ ተደርጓል፡፡

8. የሁለተኛው ዙር ጊዜያቸው ያለፈባቸው የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን የመከላከልና የማስወገድ ፕሮጀክት እ.ኤ.አ በ2003 ተጀምሮ እ.ኤ.አ በ2008 ተጠናቋል፡፡ የፕሮጀክቱ ዓላማዎች ወደ 1000 ቶን የሚጠጋ ጊዜያቸው ያለፈባቸው የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ማስወገድ፣ የተቀናጀ የተባይ መከላከያ ስልትን ማስፋፋት፣ የአገሪቱን የኬሚካል አጠቃቀም ህጎች መከለስ እና የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችና የኬሚካል መያዣ ዕቃዎች ለማስወገድ የሚያስችሉ የቴክኖሎጂ አይነቶችን መለየትና ሥራ ላይ ማዋል ናቸው፡፡
9. በሁለተኛው ዙር ፕሮጀክት በ1,055,888 ዶላር (አንድ ሚሊየን አምሳ አምስት ሺህ ስምንት መቶ ሰማንያ ስምንት ዶላር) በጀት 1100 ቶን ጊዜያቸው ያለፈባቸውን የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች በዕቅድ ለማስወገድ ተይዞ ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ ወደ 740 ቶን እንዲወገድ ተደርጓል፡፡
10. በሶስተኛው የአፍሪካ ስቶክ ፖይልስ ፕሮግራም እ.ኤ.አ በ2007 ተጀምሮ በ2010 የሚጠናቀቅ ነው፡፡ የዚህም ፕሮጀክት ዋና ዋና ዓላማዎች የተቀናጀ የተባይ መከላከያ ዘዴን ማጠናከር፣ በአንበጣና በሌሎች ተዛማጅ ወረርሽኝ ላይ መግታት የሚያስችል የመከላከል ስልት ተግባራዊ ማድረግ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ የማይመከኑ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን የማስወገድ ጥረት አስተዋጽኦ ማድረግ ነው፡፡
11. በሶስተኛው የአፍሪካ ስቶክ ፖይልስ ፕሮግራም ወደ 450 ቶን የሚሆን ፀረ-ተባይ እና 842 ቶን የተበከለ ቁሣቁስ (አፈር፣ ዘር፣ ማዳበሪያና ልዩ ልዩ የፀረ-ተባይ ማሸጊያዎችና የተበላሹ የመርጫ ማሣሪያዎች) በ103 ጣቢያዎች ቆጠራ ተካሂዷል፡፡ ፕሮጀክቱ ባለመጠናቀቁ በዕቅድ የያዛቸውን ሥራዎች ተግባራዊ ያደርጋል ተብሎ ይታሰባል፡፡

<u>የሚኒስቴር መ/ቤቱ ዓለማ፤ ሥልጣንና ተግባር</u>

<u>የግብርና ሚኒስቴር አጠቃላይ ዓላማዎች</u>

12. የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር የተቋቋመበት ዋና ዋና ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡
    - የግብርናን አመራረት ወደ ገበያ ተኮር ያመራረት ሥርዓት ማሸጋገርና የአርሶ አደሩን፣ የአርብቶ አደሩንና የከፊል አርብቶ አደሩን ገቢ በማሳደግ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት አስተዋጽኦ ማድረግ፤

- ሥር ለሰደደ የምግብ  ጥረት ተጋላጭ ለሆነው የሕብረተሰብ ክፍል የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፤
- የተፈጥሮ ሀብ ችንን በመንከባከብና በአግባቡ በመጠቀም ለግብርና ልማ ችን የሚኖረውን አስተዋፅኦ ማሳደግ፤

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር

13. የአስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣ አዋጅ ቁጥር 691/2003 ለግብርና ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ተሰጥተውታል፡፡

- የግብርናውን ዘርፍ ምርታማነት ለማሻሻል ለአርሶ አደሩ፣ ለአርብቶ አደሩ እና ለግል ባለሀብቱ የሚሰጡ የኤክስቴንሽንና የሥልጠና አገልግሎቶች እንዲስፋፉ ያደርጋል፤
- ለገበያ የሚቀርብ የግብርና ምርት የጥራት ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤
- ወደ ሀገር በሚገቡትም ሆነ ከሀገር በሚወጡ ዕጽዋት፣ አዝርዕት፣ እንስሳትና የእንስሳት ተዋጽኦ ላይ ተገቢውን የኳራንቲን ቁጥጥር ያደርጋል፤
- የእንስሳትና የእጽዋት በሽታዎች ወረርሽኝንና ተዛማች ተባዮችን ይከላከላል፤
- የተፈጥሮ ሀብት በዘላቂ የግብርና ልማት የሚጠበቅበትንና የሚለማበትን ስልት ይቀይሳል፣ ተግባራዊ የሚሆንበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
- የግብርና ግብዓት አቅርቦት፣ ሥርጭትና ግብይት አቅምን ይገነባል፣ አቅርቦቱን ያረጋግጣል፤
- የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችና የእንስሳት መድሐኒቶች አስተዳደርና ቁጥጥር ሥራዎች በአግባቡ መፈጸማቸውን ያረጋግጣል፤
- የግብርና ልማትን ለማፋጠንና የገጠር ቴክኖሎጂን ለማሻሻል የሚረዱ የማሰልጠኛ ማዕከሎችን ያቋቁማል፣ ይመራል፤
- የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ሥራዎችን ያከናውናል፣ የምግብ ዋስትና ኘሮግራም መተግበሩን ያረጋግጣል፤
- የብድር አገልግሎቶች ለአርሶ አደሮችና ለአርብቶ አደሮች የሚቀርቡበት ሁኔታ መመቻቸቱን ያረጋግጣል፤
- በግብርና ምርት ላይ ተጽዕኖ የሚያስከትሉ ወቅታዊ ሁኔታዎች ይከታተላል፣ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሥርዓት ይዘረጋል፤

- ለግብርና ልማት አጋዥ የሆኑ የአነስተኛ መስኖ ልማቶች እንዲስፋፉ ያደረጋል፤
- የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሥርዓት መዘርጋቱን ይከታተላል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣ አገራዊ መረጃ ያደራጃል፤
- የግብርና ምርምርን፣ የብዝሀ ሕይወት ጥበቃን እና ከክልሎች በተገኘ ውክልና መሠረት በፌዴራል መንግስት ሥር እንዲሆኑ የተደረጉ የግብርና ኢንቨስትመንት መሬቶችን አስተዳደር የሚመለከቱ ሥራዎች በአግባቡ እንዲከናወኑ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፡፡

<u>የእንስሳትና ዕጽዋት ጤናና ጥራት ቁጥጥርና ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት ዓላማዎች</u>

14. በሚኒስቴር መ/ቤቱ ውስጥ የተዋቀረው የእንስሳትና ዕጽዋት ጤናና ጥራት ቁጥጥርና ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት በሃገሪቱ ውስጥ በጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ የእንስሳት መድሐኒትና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ይመዘግባል ይቆጣጠራል፡፡ ለዚህም ማስፈፀሚያ የሚከተለውን ዓላማ ይዞ ይንቀሳቀሳል፡፡
    - የእንስሳትና ዕጽዋት ጤናና ጥራትን በመቆጣጠር፣ የበሽታና ተባይ ቅኝት በማካሄድ፣ የግብአት ጥራት ቁጥጥር አገልግሎትን አሰራር በማቀላጠፍና ሽፋኑን በማሳደግ የእንስሳትና እንስሳት ተዋጽኦዎች እንዲሁም የዕጽዋትና ዕጽዋት ውጤቶችን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ማሳደግ ነው፡፡

<u>የመ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅርና የሠው ኃይል</u>

15. የግብርና ሚኒሰቴር በአንድ ሚኒስቴር፣ በሶስት ሚኒስትር ዲኤታ እና በአሥራ አምስት ዳይሬክቶሬቶች የተዋቀረ ሲሆን፣ ሚኒስትር ዴኤታዎች የሚያስተዳድሯቸው ዘርፎች የግብርና ልማት ዘርፍ፣ የተፈጥሮ ሀብት ዘርፍ፣ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት እና የምግብ ዋሰትና ዘርፍ ናቸው፡፡ በግብርና ልማት ዘርፍ ሥር ከተቋቋሙት ዳይሬክቶሬቶች መካከል የእንስሳትና እጽዋት ጤናና ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ይገኝበታል፡፡ ይህ ዳይሬክቶሬት በስሩ ልዩ ልዩ የእጽዋትና የእንስሳት ባለሞያዎች አሉት፡፡ አሁን ያለው የግብርና ሚኒሰቴር የሰው ኃይል 1,417 ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ 309 ባለሙያዎች፣ 100 መለስተኛ ባለሙያዎች እና 1008 ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ናቸው፡፡

<u>የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ</u>

16. የግብርና ሚኒስቴር በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ በተቀመጠው መሠረት ከመንግስት በሚመደበለት በጀት እና ጊዜያቸው ላለፈባቸው ፀረ-ተባይ ማስወገጃ ከተለያዩ ሀገራት

ከአሜሪካ፣ ከፊንላንድ፣ ከቤልጅዬም፣ ከጃፓን፣ ከሲውዲን እና ከኔዘርላንድ እንዲሁም ከክሮፕ ፕሮቴክሽን ከሚያገኘው የገንዘብ ድጋፍ ይንቀሳቀሳል፡፡

17. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱም ባለፉት ሶስት ተከታታይ አመታት ማለትም በ2000፣ 2001 እና 2002 በጀት ዓመታት ብር 2,339,092,659.00፣ ብር 2,377,769,328.66 እና ብር 2,433,016,486.00 በቅደም ተከተሉ መሠረት የተመደበለት ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 2,167,987,836.36፣ ብር 1,797,192,248.03 እና ብር 2,258,764,361.09 ወጪ አድርጓል፡፡ ይህም በመቶኛ ሲገለጽ 93%፣ 75% እና 93% ከተፈቀደለት በጀት የተጠቀመ መሆኑን ያሳያል፡፡

18. ከላይ ከተጠቀሰው በጀት ውስጥ የእንስሳትና እጽዋት ጤናና ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ባለፉት ሶስት አመታት ማለትም በ2000፣ 2001 እና 2002 ብር 11,083,250.00፣ ብር 21,065,525.00 እና ከ24,624,621.45 የተመደበለት ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 6,634,511.46፣ ብር 18,273,584.57 እና ብር 22,571,202.84 ወጪ አድርጓል፡፡ ይህም በመቶኛ ሲገለጽ 60%፣ 87% እና 92% ከተፈቀደለት በጀት የተጠቀመ መሆኑን ያሳያል፡፡

## የኦዲቱ ዓላማ፤

19. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን በመንግስትና በግል ተቋማት ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባትና ጥቅም ላይ ለማዋል በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተዘረጋው የአመዘጋገብ፣ አጠባበቅ፣ አወጋገድ እና የመረጃ አያያዝና ቁጥጥር ሥርዓት በአግባቡ የተዘረጋ መሆኑን፣ ፀረ-ተባይ ኬሚካል በሠው ጤና እና በአካባቢ ላይ ጉዳት በማያደርስ መልኩ መጠበቁን እና ጥቅም ላይ መዋሉን፣ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች በወቅቱ ጥቅም ላይ እንዲውሉና እንዳይበላሹ አስፈላጊው የቁጥጥር እና የክትትል ሥራ መሠራቱን እና ውጤታማ መሆኑን ለማረጋገጥ ሲሆን፣ ውጤታማ ሆኖ ካልተገኘ ውጤ ማ ንዳይሆን ያደረጉትን ችግሮች በመለየት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የሚያስችል የማሻሻያ ሃሳብ (Recommendations) ለሥራ አመራሩ ለማቅረብ ነው፡፡

## የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

20. በኦዲቱ የተሸፈነው ከ2000 ዓ.ም ስከ የ2002 በጀት ዓመት የተከናወነውን የሥራ እንቅስቃሴ ነው:: ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በግብርና ሚኒስቴር ሲሆን፣ የፀረ-ተባይ ኬሚካል ምዝገባ፣ ጥበቃ እና አወጋገድን የሚመለከቱ የተለያዩ አግባብ ያላቸው መረጃዎች በመከለስ፣

ስለጉዳዩ ለሚመለከታቸው የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱን የእንስሳትና እጽዋት ጤናና ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት እና የግብርና ግብይት ዳይሬክቶሬት ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ፣ ለመስክ ሥራ በተመረጡ 4 የአበባ እርሻ አምራች ድርጅቶች፣ 12 የግል ፀረ-ተባይ አስመጪ ድርጅቶች፣ በአማራ፣ በደቡብ እና በኦሮሚያ ክልሎች 7 ዞኖች እና 18 ወረዳዎች በመገኘት ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ እና በሥፍራው ላይ በመገኘት የቀጥታ መረጃ አሰባሰብ ዘዴን (Physical Observation) በመጠቀምና ዶክመንቶችን በመከለስ ለኦዲቱ የሚያስፈልጉ ልዩ ልዩ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ እንዲሁም ጉዳዩ የሚመለከታቸው የአዳሚ ቱሉ የፀረ-ተባይ ማደራጃ አ.ማ፣ የጅማ ግብርና ምርምር ማዕከል፣ የአምቦ የእጽዋት ጥበቃ፣ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ የጅማ አዝርዕት ጥበቃ ክሊኒክ፣ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን፣ የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ማዕከል የሥራ ኃላፊዎች ቃለመጠይቅ በማቅረብ እና በሥፍራው ላይ በመገኘት የቀጥታ መረጃ አሰባሰብ ዘዴን (Physical Observation) በመጠቀም እንዲሁም ዶክመንቶችን በመከለስ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

<u>የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች</u>

21. ከላይ የተመለከተውን የኦዲት ዓላማ ለማሳካት የተመረጡት ሦስት የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) ተመርጠዋል፡፡ እነሱም፡-

1. **የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን በመንግስትና በግል ተቋማት ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባትና ጥቅም ላይ ለማዋል በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተዘረጋው የአመዘጋገብ፣ የመረጃ አያያዝና ቁጥጥር ሥርዓት ተግባራዊ መሆኑን ማረጋገጥ፣**
    1.1 የመንግስትና የግል ተቋማት የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ለማስገባት የሚኒስቴር መ/ቤቱን የቅድሚያ መስፈርቶች ባሟላ መልኩ ስለመፈቀዳቸው ማረጋገጥ፣
    1.2 የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች የመረጃ አያያዝ ሥርዓት ተግባራዊነቱን መፈተሽ፣
    1.3 ተመዝግበው ጥቅም ላይ የሚውሉ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን በሚመለከት የተዘረጋው የቁጥጥር ሥርዓት ተግባራዊ መሆኑን ማረጋገጥ፣
2. **ፀረ-ተባይ ኬሚካል በሠው ጤና እና በአካባቢ ላይ ጉዳት በማያደርስ መልኩ መጠበቁን እና ጥቅም ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን ማረጋገጥ፣**
    2.1 ፀረ-ተባይ ኬሚካል በሠው ጤና እና በአካባቢ ላይ ጉዳት በማያደርስ መልኩ መጠበቁን ማረጋገጥ፣
    2.2 የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ከቦታ ቦታ ሲጓጓዙ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ያወጣውን መስፈርት ባሟላ መልኩ መሆኑን ማረጋገጥ፣

2.3 ፀረ-ተባይ ኬሚካል ጥቅም ላይ በሚውልበት ወቅት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያለው የቁጥጥር ሥርዓት መተግበሩን ማረጋገጥ፣

3. **ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች በወቅቱ ጥቅም ላይ እንዲውሉና እንዳይበላሹ አስፈላጊው ቁጥጥር መደረጉንና የተበላሹ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ባግባቡ መከማቸታቸውንና መወገዳቸውን ማጣራት፣**

   3.1 ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ከማለፉ በፊት በወቅቱ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ

   3.2 ጊዜያቸው ያለፈባቸው ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች በተቀመጠው ደረጃ መሠረት መከማቸታቸውንና መወገዳቸውን ማጣራት፣

***የመመዘኛ መስፈርቶች*** /Evaluative Criteria/

22. ለተመረጡ ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች 52 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች የተዘጋጁ ሲሆን፣ በተዘጋጁት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችና የመመዘኛ መስፈርቶች ላይ በግብርና ሚኒስቴር ለእንስሳትና እጽዋት ጤናና ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት አስተያየት እንዲሰጡበት ቀርቦ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ የመመዘኛ መስፈርቶቹ ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ አንድ ተያይዘዋል፡፡

**የፀረ-ተባይ ምዝገባ የሥራ ሂደት መግለጫ**

- ፀረ ተባይ ውቅና ባላቸው የምርምር ተቋማት የማረጋገጫ ሙከራ ተካሂዶ በግብርና ሚኒስቴር የግምገማ ሥራ ይከናወናል፡፡
- ባሀብቶች በልዩ ፍቃድ ከውጭ አገር አስገብተው በራሳቸው ማሣ ላይ ጥቅም ላይ የሚውሉ ፀረ-ተባይ በተመለከተ በግብርና ሚኒስቴር ክትትልና ግምገማ የተደረገበት ብቃ ቸውን በማሳ ላይ ንዲረጋገጥ ይደረጋል።

ይህ ሥራ የሚከናወነው በኤዝ ቲሞች ሲሆን የተገኘውም የግምገማ ውጤት የሚፀድቀው በቦርድ (ከዘርፉ ጋር ግንኙነት ካላቸው አካላት በተወከሉ አባላት) ነው። ቦርዱ በየሶስት ወሩ በመገናኘት ውሳኔዎችን ያፀድቃል።

1. **የተገልጋይ ጥያቄ መቀበል**
   - በዚህ የሥራ ደረጃ በሀገር ውስጥ በምርምር የሚፈልቁ ዝርያዎች በግብዓትነት ንዲውሉ ለማስመዘገብ፣ በመደበኛነት የሚገቡ ፀረ ተባይ ንዲሁም ባለሀብቶች በልዩ ፈቃድ የሚያስገቧቸው ፀረ-ተባዮች በሀገር ውስጥ ለማስመዝገብ ተመራማሪው ወይም አስመጪው ጥያቄ የሚያቀርብበት የሥራ ደረጃ ነው።

2. **መረጃ መገምገም**
   - ይህ የሥራ ደረጃ በቀረበው ማመልከቻ መሠረት ለወደፊቱ ቀጣይ ሥራዎችን ለማከናወን አስፈላጊው መረጃ መሟላቱን የሚረጋገጥበት ሂደት ነው። የግምገማ ሥራውን ለማከናወን የላቦራቶሪና የመስክ ሙከራ ሥራዎች ንዲከናወኑ ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች ከማመልከቻው ጋር ተያይዘው መቅረባቸውንና ተቀባይነት ያላቸው መሆናቸውን ከህጉችና ደንቦች ጋር በማገናዘብ በሚመለከ ቸው ባለሙያዎች የማጣራት ተግባር የሚከናወንበት ነው፡፡፡

3. **የመረጃ ግምገማ ውሣኔ**
   - ይህ የሥራ ደረጃ ከላይ በሥራ ደረጃ 2 ከጥያቄው ጋር ተያይዘው የቀረቡት ደጋፊ መረጃዎች የመስክና ላብራቶሪ ፍተሻ ለማከናወን ፈቃድ ለመስጠት ጥያቄው ተቀባይነት መኖር አለመኖሩ ውሣኔ የሚሠጥበት የሥራ ደረጃ ነው።
   - ይህ ሥራ ንደ ግብዐቱ አይነት ከሚመለከ ቸው ባለሙያዎች በተውጣጣ ኤዝ ቲም የሚሠራ ተግባር ሲሆን በውሣኔው መሠረት አመልካቹ የቀረበው ደጋፊ ሠነድ ሙሉ ለሙሉ ተቀባይነት ካለው ና የተወሰኑ ማሟላት ያለባቸው ካለም ለባለጉዳዩ በመግለፅ ንዲሟላ በማድረግ ወደሚቀጥለው የሥራ ደረጃ ይተላለፋል።

4. **ለአመልካቹ መመለስ**

- በደረጃ 3 ውሣኔ መሠረት ተቀባይነት ያላገኙ ማመልከቻዎች ከነምክንያ ቸው በጽሁፍ ለአመልካች የሚገለፅበት የሥራ ደረጃ ነው፡፡

5. **ናሙና መረከብና ማከማቸት**

- ይህ የሥራ ደረጃ በምርምር የሚቀርብ (በማፍለቅ/በማላመድ) በሥራ ደረጃ 3 ተገምግሞ ተቀባይነት ካገኘ በኋላ በመስክና በላቦራቶሪ የማረጋገጫ ሙከራ ማከናወን ንዲቻል ለሙከራ የሚሆን ናሙና ከአመልካቹ በቅጽ መቀበልና የናሙናውን ግማሽ (Replication) ለወደፊቱ የተለያዩ አገልግሎት የሚሆን በቀዘቃዛ መጋዘን (Cold store) የሚከማችበት የሥራ ደረጃ ነው፡፡

- የሚቀርበው የናሙና መጠን ከ ያንዳንዱ ተወዳዳሪ ግብዓት ኩል መጠን /ክብደት/ ያላቸው ናሙናዎች በሦስት የተለያዩ መያዣዎች ተዘጋጅተው አስረካቢና ተረካቢ ፈርመውበት አንዱ ናሙና በአስረካቢው፣ ሁለተኛው ናሙና በተረካቢ መጋዘን የሚቀመጥ ሲሆን፣ ሦስተኛው ናሙና ደግሞ ሙከራውን በሚያከናውነው አካል ለሙከራ ሥራ አገልግሎት ይሆናል፡፡

6. **የማረጋገጫ ሙከራ ማከናወን**

- ይህ የሥራ ደረጃ ቀደም ብሎ በተወዳዳሪ ዝርያዎች ላይ ከተከናወነው የምርምር ውጤት መረጃ ጋር ለማመሳከርና ለማረጋገጥ የመስክና የላቦራቶሪ ሙከራ የሚደረግበት የሥራ ደረጃ ነው፡፡ ይህ ሙከራ የሚከናዉነው የተወዳዳሪ ዝርያዎች ናሙና ከመጡበት አካባቢ ጋር ተመሳሳይ ሥነ-ምህዳሮች ባላቸው አካባቢዎች ነው፡፡ የሙከራ ማሳን በተመለከተ ከምርምር ማዕከላት፣ ሌሎች ድርጅቶችና መ/ቤቶች ጋር የውል ስምምነት በማድረግና የ ነሱን ማሳ በመጠቀም ወይም በግብርና ሚኒስቴር መስሪያ ቤት በሚያዘጋጀው ማሳ ና በአርሶ አደሮች ማሳ ላይ የሚከናወን ነው፡፡

7. **የአገልግሎት ክፍያ ንዲፈጸምና ናሙና ንዲገባ ፈቃድ መስጠት**

- በተዘጋጁት ቅጾች ላይ አስፈላጊውን የአገልግሎት ክፍያ በመክፈል የፀረ-ተባይ/ማዳበሪያ ናሙና ወደ ሀገር ውስጥ ንዲያስገባ ለአመልካች ፈቃድ የሚሰጥበት የስራ ደረጃ ነው፡፡

8. **ናሙናና ገንዘብ በመረከብ ለምርምር ማዕከል መላክ**

- ይህ የሥራ ደረጃ በሥራ ደረጃ 7 ናሙና ንዲያስገባ ፈቃድ የተሠጠው አስመጪ ናሙናውን ካመጣ በ ላ ፈቃድ ለሰጠው ክፍል ሲያስረክብ ፈቃድ ሰጪው የመጣው ናሙና ከተፈቀደው ጋር ተመሣሣይ መሆኑን ካረጋገጠ በ ላ ናሙናውን በቅጽ በመረከብ ለምርምር የሚያስፈልገውን ገንዘብ በተቀመጠው መጠን መሠረት ናሙናና ገንዘብ የሚረከቡበት የሥራ ደረጃ ነው፡፡

- በፀረ-ተባይና ማዳበሪያ ላይ ማረጋገጫ ሙከራ የሚያከናውንለትን ማዕከል /ተቋም/ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመርጥ ሲሆን ከባለጉዳይ የተሰበሰበውን ገንዘብና ናሙና ከደብዳቤ ጋር በማያያዝ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ምርምሩን ወደሚያከናውነው ማዕከል /ተቋም/ ይልካል፡፡

**9. ምርምር ማከናወን**

**9.1 ፀረ-ተባይ፣ ማዳበሪያና ወዘተ**

- የምርምር ተቋማት በመደበኛ ስራቸው ከሚያከናውኗቸው ሙከራዎች በተጨማሪ ከግብርና ሚኒስቴር ጋር በሚያደርጉት/ ባላቸው ስምምነት መሰረት ከዓመ ዊ ሰብሎች (Annual Crops) ውጭ የሆኑ ፀረ-ተባይ፣ ማዳበሪያዎችንና ሌሎች የማረጋገጫ ሙከራ ያከናውናል፡፡ ምርምር የሚያካሂደው ተቋም የሚካሄድበትን ቦ (ዎች) ለግብርና ሚኒስቴር በደብዳቤ የሚያሳውቅ ሲሆን የሚኒስቴሩ ኬዝ ቲም ሙከራውን ይገመግማሉ፡፡

**10 ልዩ ፈቃድ ለሚያስፈልጋቸው ግብዓቶች ፈቃድ መስጠት**

- ይህ የሥራ ደረጃ ለውጭ ገበያ ተፈላጊ የሆኑ የምርት ዓይነቶችን ለማምረት የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን ባለሀብቶች ወደ ሀገር ውስጥ አስገብተው በራሳቸው ማሣ ላይ ብቻ ለመጠቀም የማስገቢያ ፈቃድ ለማዳበሪያና ፀረ-ተባይ የሚሰጥበት የሥራ ደረጃ ነው፡፡ ነዚህም ከአሁን በፊት በሀገራችን ጥቅም ላይ ያልዋሉና ያልተመዘገቡ ግብዓቶች ናቸው፡፡

**11 የመስክ ግምገማ ማከናወን**

- በተቆጣጣሪው አካል የሚከናወነውን የዝርያ የማረጋገጫ ሙከራ፣ በሌሎች የምርምር ተቋማት የሚከናወነውን የፀረ ተባይ፣ ማዳበሪያ፣ የ ንስሳት ዝርያዎችንና ሌሎች ግብዓቶችን ሙከራና በባለሃብቶች በልዩ ፈቃድ ከውጭ አገር ገብተው በሀገር ውስጥ ተመርተው ለውጭ ገበያ የሚውሉ ግብዓቶችን በአምራቾች ማሳ ላይ በግብርና ሚኒስቴር ባለሙያዎች በቴክኒካል ማንዋል መሰረት የሚከናወን የግምገማ ተግባር ነው፡፡
- የመስክ ግምገማው ከተጠናቀቀ በኋላ ከመስክና ላቦቶሪ የተገኙ ውጤቶችን በማሰባሰብ የቀረቡ መረጃዎችን ከግምገማው ውጤት ጋር በማገናዘብ፣ በመተንተንና በማጠናቀር ስለግብዓቶች ውጤ ማነት የውሳኔ ሀሳብ በማቅረብ ሪፖርት የሚዘጋጅበት የሥራ ደረጃ ነው፡፡

**12. የግምገማ ውጤት ውሳኔ**

- ይህ የሥራ ደረጃ የተከናወኑትን የሙከራ ውጤቶች ና ከማመልከቻዉ ጋር የቀረቡትን የጽሑፍ መረጃዎች (Data) በማገናዘብና በማነጻጸር የሚመለከ ቸው ባለሙያዎች በሚገኙበት ስብሰባ ውይይት ተካሂዶ የቀረቡት ተወዳዳሪ ግብዓቶች ለምዝገባ ተቀባይነት ማግኘ ቸውንና አለማግኘ ቸውን ውሳኔ የሚሰጥበት የሥራ ደረጃ ነው፡፡ ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ባለሙያዎችና ከአመልካቾች በተጨማሪ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚመርጣቸውና ከግብዓቶች አጠቃቀም ጋር ግንኙነት ካላቸው መሥሪያ ቤቶች የተወከሉ ባለሙያዎች (የቦርድ

አባላት) በስብሰባው የሚሳተፉ ሲሆን፣ ውሳኔውም ከህጎች በገምጋሚ ባለሙያዎችና በቦርድ አባላት የሚወሰን ይሆናል። ስብሰባው በየሶስት ወሩ ለሁለት ቀናት ይካሄዳል።

**13 ከግብዓትነት ዝርዝር ውስጥ መሰረዝ/ ንዳይውል ማድረግ**

- አዲስ ለግምገማ የቀረበም ሆነ ቀደም ብሎ ተመዝግቦ በጥቅም ላይ የነበረ ግብዓት የሚጠበቅበትን ጠቀሜ  የማይሰጥ ሆኖ ሲገኝ ከግብዓትነት የሚወገድበት የስራ ደረጃ ነው።

**14. መመዝገብ፣ ሰርተፊኬት መስጠትና ውጤት የማሳወቅ ተግባር**

- በዚህ የሥራ ደረጃ ተገምግመው የፀደቁ ግብዓቶች ጥቅም ላይ  ንዲውሉ ለግብዓቶች የምዝገባ ሰርተፊኬት መስጠት፣ በድረ-ገጽ ማሠራጨትና በዓመቱ የተመዘገቡ ግብዓቶችን ዝርዝር በህትመት በማዘጋጀት ለተጠቃሚዎች  ንዲደርሱና ጥቅም ላይ  ንዲውሉ የማሳወቅ ሥራ ይከናወናል። አንድ ጊዜ የተመዘገበ ፀረ-ተባይ የአገልግሎት ዘመኑ ለሶስት ዓመት ሲሆን ለተጨማሪ ሶስት ዓመት አግልግሎት  ንዲሰጥ በቅጽ ጥያቄ ሲቀርብ ሙከራ ማካሄድ ሳያስፈልግ በድጋሚ ተመዝግቦ በግብዓትነት ይቆያል። ለቀጣይ  ድሳት ከተፈለገ ግን የማረጋገጫ ሙከራ መካሄድ አለበት።


**15. ግብረ መልስ**

- በየደረጃው የሚገኙ መረጃዎችን፣ ጥቆማዎችና አስተያየቶችን በየደረጃው ያሉ ሰራተኞች በማጠናቀር ለሚመለከተው አካል ማስተላለፍ፣ ማስተካከያ  ርምጃ መውሰድና ወደ መረጃ ቋት መላክ ይጠበቅባቸዋል።

**16. ተመዝግበው በጥቅም ላይ ያሉ ፀረ-ተባይ፣ ማዳበሪያ  ና ሌሎች ግብዓቶችና መገምገም**

- ጠቀሜ ቸው በምርምር ከተረጋገጠ በኋላ ከ ፅዋትና ከ ንስሳት ዝርያዎች ውጭ የሆኑ ግብዓቶች በጥቅም ላይ  ያሉ ከግብረ መልስ በሚገኘው መረጃ መሰረት በውጤ  ማነ  ቸው ላይ ጥርጣሬ ሲኖር ግብዓቶችን  ንደገና የመገምገም ሥራ የሚከናወንበት የሥራ ደረጃ ነው። ይህ የስራ የሚከናወነው ውጤ  ማነ  ቸው የቀነሱትን ግብዓቶች ናሙና ከማሳ፣ ከመጋዘንና ከገበያ ላይ በማሰባሰብ የማረጋገጫ ሙከራ  ንደገና በማካሄድና በሚቀጥሉት የሥራ ደረጃዎች የሚያስፈልጉ ሥራዎችን በማከናወን ነው።

## የፀረ-ተባይ ምዝገባ የሥራ ሂደት መግለጫ



## የብቃት ኢንስፔክሽን የሥራ ሂደት መግለጫ

የብቃት ማረጋገጫ ኢንስፔክሽን የሥራ ሂደት የሚሠራበት ምክንያት ና አስፈላጊነት በግብርና ግብዓትና ምርት ንግድ ሥራ ለመሰማራት በግብርና ሚኒስቴር በተቀመጠው መስፈርት (መመሪያ ቁ. 1) መሰረት ከንግድ ሚኒስቴር ወይም ቢሮ ፈቃድ አውጥተው ወደ ተግባር ከገቡ በኋላ በገቡት ውለ መሠረት ስራቸውን በአግባቡ ለመስራ ቸው ና የግብርና ምርት ጥራት ላይ አሉ ዊ ተፅዕኖ አለማሣደራቸውን ምስክርነትና ቁጥጥር የሚደረግበት የሥራ ሂደት ነው።

የብቃት ማረጋገጫ ኢንስፔክሽን ሥራ የሚከናወነው ከተለያዩ ዲስፕሊን በተውጣጡ ኬዝ ቲሞች አማካኝነት ነው።

- ግብዓት አስመጭ፣ ጅምላ አከፋፋይና ቸርቻሪ ንዲሁም ዮርጭትና የ ጥናት አገልግሎት የሚሰጥ - የሰብል ጥበቃ ባለሙያ፣ ኬሚስትና አግሮኖሚስት

### 1. አመ ዊ ዕቅድና ፕሮግራም ማዘጋጀት

- ይህ ሥራ ዓመ ዊ ፕሮግራም ወጥቶለትና ንዳስፈላጊነቱ ከንግድ ሚኒስቴር /ከክልል ንግድ ቢሮ በሚገኘው መረጃ /የምዝገባ ዝርዝር/ በደብዳቤ ወይም ድረ-ገጽ ሲገለጽና ከሌሎች ምንጮች የሚገኙ መረጃዎችን በመጠቀም ዳሰሳ ለማካሄድ ዝርዝር ቅድ የሚዘጋጅበት ነው።
- ይህ ሥራ ንደ ግብዓቱና የምርቱ ዓይነት በሚመለከ ቸው የኬዝ ቲም አባላት የዓመቱ ፕሮግራም ይዘጋጃል።

### 2. ቅድመ ሁኔ ዎችንና ሥራ በትክክል የተሰራ መሆኑን በቦ ው ማረጋገጥ

- በዚሁ ደረጃ ንደ ባለሙያዎቹ (Case Team) ንግድ ፈቃድ በተመዘገበበት/ በወጣበት ድርጅት አድራሻ መሠረት በቦ ው በመገኝት ከየት መ/ቤት ንደመጡና ለምን ንደመጡ ለድርጅቱ ባለቤት ( ላፊ/ተወካይ) ራሳቸውን በማስተዋወቅ ይገልፃሉ።
- ወደ ሥራ የገቡበትን የንግድ ፈቃድ ያጣራሉ/ይመለከ ሉ፣
- የሥራውን ሂደት ከመጀመሪያ ስከ መጨረሻ፣ የሚጠቀሙበትን መሣሪያ ጥራትና ብቃት፣ ለሥራው የተመደበውን ባለሙያ ውቀትና ክህሎት በመገምገምና በማየት አስፈላጊውን መረጃ በቅጽ ይመዘግባሉ።

### 3. ውሳኔ መስጠት

- ይህ ደረጃ ውሣኔ የሚሰጥበትና ባለጉዳዩ በገባው የውዴ ግዴ መሠረት በትክክል መስራቱ የሚረጋገጥበት ስለሆነ ባለሙያዎቹ በጉብኝቱ ወቅት በግላቸውና በጋራ በያዙት ማስ ወሻ መሠረት ሁኔ ው ቀላልና የጋራ ግንዛቤ የተያዘበት ከሆነ ለድርጅቱ ላፊ ባለቤት /ተወካይ/ የወሰዱትን ግንዛቤ ዛው ይገለፅለ ል።

- ወይም የግንዛቤ አያያዙ የኬዝ ቲሙን ባለሙያዎች የመረጃ ትንተና ና ውይይት የሚጠይቅ ከሆነ ወደ ቢሮ በመመለስ ሰፊ ውይይት ተደርጎ የተስማሙበት የውሣኔ ሃሳብ ይያዛል:: ካልተስማሙ በአብላጫ ድምጽ ውሣኔ ያገኛል::

4. <u>ርምጃ መውሰድ</u>

- ጉብኝት የተደረገበት ድርጅት በገባው የውዴ ግዴ መሠረት የሠራ ንዳልሆነ ሲረጋገጥ ንደ ጥፋቱ ክብደትና ቅለት ንዲሁም ሥራው በንግዱና በምርት ጥራቱ ላይ ያሣደረ ባለው አደጋ መጠን ባሉት ህጎች መሰረት በተቀመጠው የ ርምጃ ርከን አስፈላጊው ርምጃ ንዲወሰድ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያደርጋል::

5. <u>የብቃት ማረጋገጫ ደብዳቤ መስጠት</u>

- በውሣኔው መሠረት ድርጅቱ በቂ መሆኑ ከተረጋገጠ በስራው ንዲቀጥል ይደረጋል:: አፈጻጸሙም አጥጋቢ ከሆነ የጥሩ ደረጃ ተመዝጋቢ (Good-List) ውስጥ ንዲገባ በማድረግ በተዘጋጀው ሰርተፊኬት መሰረት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል::

6. <u>ክትትል፣ ግምገማ፣ ግብረ መልስና መረጃ</u>

- በሥራው ላይ ከደንበኞችና ከባለድርሻዎች የሚመጡ ጥቆማዎችንና መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፣ ይገመግማል:: የማሻሻያ ርምጃዎችን ይወስዳል:: መረጃውን ያሰራጫል ብሎም ወደ መረጃ ቋት ይተላለፋል::

7. <u>በየደረጃው ያሉ አስፈጻሚ አካላት የሥራ ድርሻ</u>


**7.1 በፌዴራል ደረጃ**

ይህን ሥራ ለመስራት በፌደራል ንግድ ሚኒስቴር ይሁን በክልል ንግድ ቢሮ ፈቃድ አውጥተው ከአንድ ክልል በላይ የሚያመርቱ/የሚያከፋፍሉ ንዲሁም ከውጪ ግብዓት ለንግድ የሚያስመጡ በፌደራል ግብርና ሚኒስቴር ጽ/ቤት ቁጥጥሩ ያካሄዳል::

**7.2 በክልል ደረጃ**

ከክልል ንግድ ቢሮ ፈቃድ አውጥተው ለክልሉ ብቻ የሚያመርቱ፣ የሚያከፋፍሉና የሚቸረችሩ በክልል ግብርና ቢሮ ቁጥጥሩ ይካሄዳል:: ሥራው በተለያየ ርከን ቢሰራም መረጃ በመረጃ መረብ አማካኝነት ለሚመለከተው ሁሉ ይተላለፋል::

## የብቃት ኢንስፔክሽን የሥራ ሂደት



# ክፍል ሁለት

# ግኝቶች

**የፀረ-ተባይ መጋዘኖች አገነባብ ደረጃውን**

**የጠበቀ መሆኑን በተመለከተ፣**

23. የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ማከማቻ መጋዘኖች በሚገነቡበት ወቅት ከጠንካራ ማቴሪያሎች (Galvanized iron, cement stone, brick etc) እና የመጋዘኑ ስፋት ከ50 ስኩዌር ሜትር ያላነሠ፣ የመጋዘኑ መሬት ከሲሚንቶ የተሠራ፣ የበሩ መጠን ቢያንስ 3 ሜትር ስፋት X 12 ሜትር ርዝመት፣ ከመሬት እስከጣሪያው ያለው ርዝመት ቢያንስ 3 ሜትር፣ በቂ የአየር ማስገቢያ (Ventilation)፣ የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ መሰጫ እና የእሳት አደጋ መከላከያ አሟልተው ሊገነቡ ይገባል፡፡

24. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት 12 የግል ፀረ-ተባይ ኬሚካል አስመጪ ድርጅቶች ውስጥ 2(17%) የሚሆኑት ጋልቫናይዝድ በሆነ ብረት፣ በሲሚንቶ ድንጋይ ወይም በጡብ ያልተሰሩ መሆኑ፣ 1(8%) የሚሆነው የመጋዘኑ ስፋት ከ50 ስኩዌር ሜትር ያነሰ መሆኑ፣ 1(8%) የሚሆነው የመጋዘኑ መሬት ከሲሚንቶ የተሠራ አለመሆኑ፣ 1(8%) የሚሆነው የበሩ መጠን 3 ሜትር ስፋት X 12 ሜትር ርዝመት የሌለው መሆኑ፣ 1(8%) የሚሆነው ከመሬት እስከጣሪያው ያለው ርዝመት 3 ሜትር የማይሞላ መሆኑ፣ 2(17%) በቂ የአየር ማስገቢያ (Ventilation) የሌላቸው መሆኑ፣ 6(50%) የሚሆኑት የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ መስጫ የሌላቸው መሆኑ እና 2(17%) የሚሆኑት የእሳት አደጋ መከላከያ መሣሪያ የሌላቸው መሆኑን ለመመልከት ተችሏል፡፡

25. በናሙና ተመርጠው በታዩ የአማራ፣ የኦሮሚያ እና የደቡብ ክልሎች፣ ዞኖች እና ወረዳዎች እንዲሁም የሊሙ ኮሳ ቡና ተክል እርሻ ልማት ድርጅት ውስጥ ከሚገኙ 20 የፀረ-ተባይ ኬሚካል መጋዘኖች ውስጥ 9(45%) የሚሆኑት ጋልቫናይዝድ በሆነ ብረት፣ በሲሚንቶ፣ በድንጋይ ወይም በጡብ ያልተሰሩ መሆኑ፣ 5(28%) የሚሆኑት የመጋዘናቸው ስፋት ከ50 ስኩዌር ሜትር ያነሰ መሆኑ፣ 5(28%) የሚሆኑት የመጋዘናቸው መሬት ከሲሚንቶ የተሠራ አለመሆኑ፣ 7(35%) የሚሆኑት የበራቸው መጠን 3 ሜትር ስፋት X 12 ሜትር ርዝመት የሌላቸው መሆኑ፣ 3(15%) የሚሆኑት ከመሬት እስከጣሪያው ያለው ርዝመት 3 ሜትር የማይሞላ መሆኑ፣ 11(55%) በቂ የአየር ማስገቢያ (Ventilation) የሌላቸው መሆኑ፣ 19(95%) የሚሆኑት የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ መስጫ የሌላቸው መሆኑ እና 20(100%) የሚሆኑት የእሳት አደጋ መከላከያ መሣሪያ የሌላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

26. ከዚህም በተጨማሪ በናሙና ካየናቸው አራት የአበባ እርሻ ድርጅቶች ውስጥ 1(25%) የመጋዘኑ ስፋት ከ50 ስኩዌ ሜትር ያነሰ መሆኑ፣ 2(50%) የሚሆኑት የበር መጠናቸው 3 ሜትር ስፋት X 12 ሜትር ርዝመት የሌላቸው መሆኑ እና 1(25%) የሚሆነው በቂ የአየር ማስገቢያ (Ventilation) የሌለው መሆኑን ለመመልከት ተችሏል፡፡

27. ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች አስመልክቶ የአበባ እርሻ ድርጅቶች የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ማከማቻ መጋዘኖች በምን መልኩ መሠራት እንዳለበት ወይም ምን መምሰል እንዳለበት የግብርና ሚኒስቴር ባለሙያዎች እንዳላሳወቋቸው ገልፀዋል፡፡ የክልል፣ የዞን እና የወረዳ ግብርና የሥራ ኃላፊዎች ደግሞ ችግሩ የተከሰተው በአቅም ውስንነት እና በትኩረት ማነስ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

28. ይህንንም በተመለከተ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የግብርና ሚኒስቴር ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የአበባ እርሻዎች የሚያስመጡት የፀረ-ተባይ ኬሚካል መጠን በጣም አነስተኛና ለራሳቸው ብቻ የሚጠቀሙበት በመሆኑ ትልቅ የፀረ-ተባይ መጋዘን እንዲኖራቸው እንደማይጠበቅባቸው፣ በክልሎች የሚገኙ የፀረ-ተባይ ኬሚካል መጋዘኖች ደግሞ በአብዛኛው የግብርና ሚኒስቴር ሲሆኑ እነዚህም ለወረርሽኝ መከላከያ ለሚውሉ ፀረ-ተባይ ኬሚካል ማስቀመጫ በመሆናቸው በአብዛኛው ለፀረ-ተባይ ኬሚካል ማከማቻ መጋዘንነት የተቀመጠውን መስፈርት ያሟሉ ቢሆንም አንዳንድ አካባቢ ችግር ሊኖር እንደሚችል ገልፀዋል፡፡

29. የሥራ ኃላፊው ከላይ የተገለፀውን መልስ ቢሰጡም በኦዲት ወቅት እንዳረጋገጥነው በ2009 እ.ኤ.አ የመግቢያ ፈቃድ ተሰጥቷቸው የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ካስገቡ የአበባ እርሻ አምራች ድርጅቶች ውስጥ ማለትም የጎልደን ሮዝ 13570 በሊትርና በኪሎ ግራም፣ የኦሮሚያ ወንደርስ 9982 በሊትርና በኪሎ ግራም እና የስኘሪት 780 በሊትርና በኪሎ ግራም የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ያስገቡ በመሆኑ የሚያስመጡት የፀረ-ተባይ መጠን አነስተኛ እንዳልሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡ እንዲሁም የኦዲት ቡድኑ በመስክ ሥራ ተዘዋውሮ በተመለከታቸው የክልል፣ የዞን እና የወረዳ ግብርና ቢሮ የፀረ-ተባይ ማከማቻ መጋዘኖች ያሉበት ሁኔታ አሳሳቢ መሆኑንና በፀረ-ተባይ ኬሚካል መከላከልና ማስወገድ የመጀመሪያ ዙር ኘሮጀክት ማጠቃለያ ሪፖርት (Terminal report) ገጽ 4 ላይ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ጊዜያቸው እንዲያልፍባቸው የሚያደርገው ዋነኛ ምክንያቱ ደረጃውን ባልጠበቀ መጋዘን ውስጥ መከማቸታቸው መሆኑ ተገልጿል፡፡

30. በመሆኑም የፀረ-ተባይ ኬሚካል ማከማቻ መጋዘኖች ደረጃውን ባልጠበቀ ሁኔታ መገንባታቸው የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን የአገልግሎት እድሜ (Shelf life) እንዲያጥር፣ የፍቱንነት ደረጃቸው እንዲቀንስ እንዲሁም በሰዎች እና በአካባቢ ላይ ጉዳት እንዲያደርሱ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡




ፎቶ 1 የፀረ-ተባይ መጋዘኑ ወለሉ አፈር መሆኑን የሚያሣይ ፎቶ




ፎቶ 2 የፀረ-ተባይ መጋዘኑ ጠባብ እና በቂ የአየር ማስገቢያ የሌለው መሆኑን የሚያሳይ ፎቶ




ፎቶ 3 ሙሉ በሙሉ የፀረ-ተባይ የመጋዘን ደረጃ ያሳሚሳ መሆኑን የሚያሳይ ፎቶ

## *<u>የፀረ-ተባይ መጋዘኖች ከሠዎችና ከእንስሳት መኖሪያ</u>*

## *<u>አካባቢ ርቀው መሠራታቸውን በተመለከተ፣</u>*

31 *የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ማከማቻ መጋዘኖች ከመስራታቸው በፊት የስጋት ትንተና በማካሄድ ከሠዎች ከእንስሳት እና ውሀ ከሚገኝበት ቦታ ርቀው ሊሠሩ ይገባል፡፡*

32 *የፀረ-ተባይ ማከማቻ መጋዘኖች ከመሠራታቸው በፊት የስጋት ትንተና የማይደረግ መሆኑን በኦዲት ወቅት በተደረገው የሠነድ ክለሣ እና ከሚመለከታቸው የግብርና ሚኒስቴር ኃላፊዎች ጋር በተደረገ መጠይቅ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡*

33 *በናሙና ተመርጠው ከታዩ* 12 *የግል ፀረ-ተባይ አስመጪ ድርጅቶች ውስጥ* 3(25%) *የሚሆኑት ሠዎች በሚኖሩበት አካባቢ የተሰሩ መሆኑ፣* 2(17%) *እንስሳት በአካባቢው የሚገኙ መሆኑን እና፣* 2(17%) *በአቅራቢያው ውሃ መኖሩን ለመመልከት ተችሏል፡፡*

34 *በናሙና ተመርጠው ባየናቸው በአማራ፣ በኦሮሚያ እና በደቡብ ክልሎች በ*7 *ዞኖች እና በ*18 *ወረዳዎች ውስጥ በሚገኙ የግብርና ቢሮዎች እና የሊሙ ቡና ተክል ልማት ድርጅት የፀረ-ተባይ መጋዘኖች ውስጥ* 18(90%) *የሚሆኑት ሠዎች በሚኖሩበት አካባቢ እና መስሪያ ቤት ቅጥር ጊቢ ውስጥ የተሠሩ መሆናቸው፣* 2(10%) *የሚሆኑት እንስሳት በአካባቢው የሚገኙ መሆኑን ባደረግነው የመስክ ጉብኝት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡*

35 *ይህንንም ሁኔታ በግብርና ሚኒስቴር የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የፀረ-ተባይ ኬሚካል ማከማቻ መጋዘኖች ከመገንባታቸው በፊት የሚሠራ የስጋት ትንተና አለመኖሩን እና*

በዚህ መልኩ የተገነቡ የፀረ-ተባይ መጋዘኖች አለመኖራቸውን፣ ነገር ግን ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፀረ-ተባይ መጋዘን ከመኖሪያ አካባቢ፣ ከምንጭ ውሀ፣ ከሆስፒታሎች ወዘተ የራቀ መሆን እንደለበት የብቃት ማረጋገጫ ሲሰጥ ይህንኑ ከግምት ባስገባ ሁኔታ የሚሰጥ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

36 ሆኖም በኦዲቱ ወቅት የተሰበሰቡት መረጃዎች የሚያሳያዩት የፀረ-ተባይ ማከማቻ መጋዘኖች ሠዎች፣ እንስሳት እና የገፀ ምድር ውሀ ባሉበት አካባቢ ተገንብተው መገኘታቸውን ነው፡፡ ይህም ሁኔታ በህብርተሰቡና በአካባቢ ላይ ጉዳት ሊያስከትል የሚችል መሆኑ ይታወቃል፡፡




ፎቶ 4 የፀረ-ተባይ መጋዘኑ ሠዎች በሚኖሩበት ቅጥር ጊቢ ውስጥ መሆኑን የሚያሳይ ፎቶ




ፎቶ 5 በፀረ-ተባይ መጋዘኑ አካባቢ እንስሳት መኖሩን የሚያሳይ ፎቶ




ፎቶ 6 የፀረ-ተባይ መጋዘኑ ትምህርት ቤት የሚገኝበት አካባቢ መሆኑን የሚያሳይ ፎቶ

## <u>የፀረ-ተባይ ኬሚካል መከላከያ ቁሳቁስ ለሠራተኞች</u>

### <u>የተሟላ መሆኑን በተመለከተ፣</u>

37 የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን የሚያስመጡ ድርጅቶችና የፀረ-ተባይ ተጠቃሚዎች ለሠራተኞቻቸው የመከላከያ ልብስ፣ ጫማዎች፣ ጓንት እና የመተንፈሻ አካላት መሸፈኛ ቁሳቁሶችን ማሟላት ይኖርባቸዋል፡፡

38 በናሙና ተመርጠው ከታዩ 12 የግል ፀረ-ተባይ አስመጪ ድርጅቶች ውስጥ 4 (33%) የሚሆኑት ሠራተኞቻቸው ጓንት የማይጠቀሙ መሆኑ፣ 7 (58%) የሚሆኑት ቦት ጫማ የማይጠቀሙ መሆኑን፣ 6(50%) የሚሆኑት ቱታ የማይጠቀሙ መሆኑ፣ 5(42%) የሚሆኑት የአይን መነጽር የማይጠቀሙ መሆኑ፣ 5(42%) የመተንፈሻ አካላት መሸፈኛ የማይጠቀሙ መሆኑ እና ፀረ-ተባይ ኬሚካል ለሚያወርዱና ለሚጭኑ ጊዜያዊ ሠራተኞቻቸው የመከላከያ ትጥቅ እንደማያሟሉ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

39 በናሙና ተመረጠው በታዩት የአማራ፣ የኦሮሚያ እና የደቡብ ክልሎች፣ ዞኖች እና ወረዳዎች እና የሊሙ ኮሳ ቡና ተክል እርሻ ልማት ድርጅት ውስጥ ከሚገኙ 20 የግብርና ተቋማት ፀረተባይ ተጠቃሚዎች 17(85%) የሚሆኑት ጓንት የማይጠቀሙ መሆኑ፣ 17(85%) የሚሆኑት ቦት ጫማ የማይጠቀሙ መሆኑ፣ 17(85%) የሚሆኑት ቱታ የማይጠቀሙ መሆኑ፣ 17(85%) የሚሆኑት የአይን መነጽር የማይጠቀሙ መሆኑ፣ 17(85%) የመተንፈሻ አካላት መሸፈኛ የማይጠቀሙ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

40 ይህንንም በተመለከተ የሚመለከታቸውን የክልል፣ የዞን እና የወረዳ ግብርና ቢሮ የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ይህ ሊሆን የቻለው ለጉዳዩ ትኩረት ባለመሰጠቱ፣ ያቅም ግንባታ ሥራ በበቂ ሁኔታ የተሠራ ባለመሆኑ እና በበጀት እጥረት ምክንያት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

41 የፀረ-ተባይ አስመጪዎች እና ተጠቃሚዎች ለሠራተኞቻቸው አስፈላጊውን የመከላከያ ቁሣቁስ አለማሟላታቸው በሰው ሕይወት ላይ ከፍተኛ አደጋ ሊያስከትል እንደሚችል ይታመናል፡፡




ፎቶ 7 የፀረ-ተባይ መከላከያ ቁሳቁስ ሳይጠቀሙ ፀረ-ተባይ ኬሚካል ስመጠቀም ሲያወጡ የሚያሳይ ፎቶ




ፎቶ 8 የፀረ-ተባይ መከላከያ ቁሳቁስ ሳይጠቀሙ ፀረ-ተባይ ኬሚካል ስመጠቀም ሲያወጡ የሚያሳይ ፎቶ

**የፀረ-ተባይ ኬሚካል መያዣዎች ለአጠቃቀም**

**አመቺ መሆናቸውን በተመለከተ፣**

42. ማናቸውም ማሸጊያ ፀረ-ተባዩ በሚጓጓዝበት፣ በሚከማችበት፣ ለገበያ በሚቀርብበት፣ በሚከፋፈልበትና ጥቅም ላይ በሚውልበት ጊዜ መያዣቸው አደጋ በማያስከትል እና በሚያመች ሁኔታ ዲዛይን ሊደረግ ይገባል፡፡

43. ለወረርሽኝ አገልግሎት ከውጭ ሀገር የሚገቡትም ሆነ በአዳሚ ቱሉ የፀረ-ተባይ ማደራጃ የሚቀርቡ ፀረ-ተባይ ኬሚካል መያዣ ዕቃዎች ባብዛኛው በበርሜል የሚዘጋጁ በመሆናቸው ፀረ-ተባዩን ለመጠቀም የማቀናነሻ መሣሪያዎች እና የመከላከያ ትጥቅ ባልተሟሉባቸው አካባቢዎች በሠራተኞች ላይ ችግር እየፈጠረ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በኦዲቱ ወቅት በመስክ ሥራ ተዘዋውረን በተመለከትናቸው የአማራ ክልል ግብርና ቢሮ፣ በአማራ ክልል የአቸፈር ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት፣ በኦሮሚያ ክልል የምዕራብ ሸዋ አምቦ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት እና በደቡብ ክልል የጉራጌ ዞን የቀቤና ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ከበርሜል ወደ ሌሎች እቃዎች ሲያቀናንሱ የመከላከያ ቁሣቁስ እና ማቀናነሻ መሣሪያ ባለመሟላቱ ለአደጋ እየተጋለጡ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

44. ስለጉዳዩ በግብርና ሚኒስቴር የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ለወረርሽኝ የሚመጡ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ብዙውን ጊዜ በእርዳታ የሚመጡ ስለነበሩ መጠናቸውን መወሰን እንደሚያስቸግር ሆኖም የፀረ-ተባይ ኬሚካሎቹ ጥቅም ላይ በሚውሉበት ጊዜ የመከላከያ ትጥቆችና ፀረ-ተባይ ኬሚካሉን ቀናንሶ ለመጠቀም የሚያስችሉ የተለያዩ ዘዴዎች ሥራ ላይ የሚውሉ በመሆኑ የፀረ-ተባይ ኬሚካል ርጭት በሚደረግበት ጊዜ ተገቢው ጥንቃቄ እንደሚደረግ እና በአሁኑ ጊዜ በአገር ውስጥ ፀረ-ተባይ ኬሚካል ማዘጋጀት የተጀመረ ስለሆነ ችግሩ በቀጣይነት የሚቃለል እንደሚሆን ገልፀዋል፡፡

45. የፀረ-ተባይ ኬሚካል መያዣዎች በአብዛኛው በበርሜል የሚዘጋጁ፣ ለአጠቃቀም አመቺ ያልሆኑ እና የማቀናነሻ መሣሪያዎች ባልተሟሉባቸው አካባቢዎች የፀረ-ተባይ ኬሚካሉን በሚያከፋፍሉ በአንዳንድ የክልል፣ የዞን እና የወረዳ ሠራተኞች ላይ የጤና ጉዳት እያስከተለ መሆኑ ታውቋል፡፡

**የፀረ-ተባይ ኬሚካል ባህሪ የሚገልጽ መለያ (labeling)**

**ተሟልቶ የማይለጠፍ መሆኑን በተመለከተ፣**

46. መንግስታዊና የግል ፀረ-ተባይ አስመጪዎች የኬሚካሉን የወል መጠሪያ፣ የድብልቅ መጠን፣ የአጠቃቀም መመሪያ፣ ፀረ-ተባዩ ጥቅም ላይ ከዋለ በኋላ አደጋ እንዳያስከትል መቆየት የሚያስፈልግበትን ጊዜ፣ የአለም የጤና ጥበቃ ድርጅት በወሰነው ምደባ መሠረት አደገኛነቱን የሚያስጠነቅቅ የጽሑፍና ስዕላዊ መግለጫ፣ በአደጋ ጊዜ ሊወሰድ የሚገባውን የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ አሠጣጥ፣ የተመረተበት ቀን እና የአገልግሎት እድሜውን በሚያሳይ መልኩ በፀረ-ተባይ ኬሚካል ማሸጊያዎች ላይ መለጠፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡

47. በናሙና የተመረጡ 12 የፀረ-ተባይ አስመጪ ድርጅቶች መለያው የሚጠይቀውን መስፈርት አሟልተው ተገኝተዋል፡፡

48. ሆኖም በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ የአበባ እርሻዎች መካከል ስኘሪት ፍላወር፣ጐልደን ሮዝ፣ ኦሮሚያ ወንደርስ የፀረ-ተባይ ኬሚካሉን ባህሪ የሚገልጽ ጽሁፍ መመሪያው በሚያዘው በአማርኛና በእንግሊዝኛ መፃፍ ሲገባቸው በሌላ ቋንቋ ማለትም በቻይንኛ እና በስዋህሊ ተጽፎ ተገኝቷል፡፡

49. ይህንንም በተመለከተ በግብርና ሚኒስቴር ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ከላይ የተገለፀው ችግር አልፎ አልፎ እንደሚከሰት አምነው የማስተካከያ እርምጃዎች እየተወሰዱ መሆኑን እና ችግሩን የፈጠረው ለአበባ ልማት የሚውሉት ፀረ-ተባዮች በልዩ ሁኔታ (በልዩ አሠራር) ስለሚገቡ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

50. መለያውን (labeling) በመመሪያው መሠረት በግልጽ በአማርኛና በእንግሊዝኛ አለመገለጹ የፀረ-ተባይ ኬሚካሉን የወል መጠሪያ እና የድብልቅ መጠን፣ የአጠቃቀም መመሪያ፣ ፀረ-ተባዩ ጥቅም ላይ ከዋለ በኋላ አደጋ እንዳያስከትል መቆየት የሚያስፈልግበትን ጊዜ፣ የአለም የጤና ጥበቃ ድርጅት በወሰነው ምደባ መሠረት አደገኛነቱን የሚያስጠነቅቅ የጽሑፍና ስዕላዊ መግለጫ፣ በአደጋ ጊዜ ሊወሰድ የሚገባውን የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ አሠጣጥ የተመረተበትን ቀን እና የአገልግሎት እድሜውን በግልጽ ለማወቅ ባለማስቻሉ በተጠቃሚው ላይ አደጋ ሊያስከትል ይችላል፡፡

<u>ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ የፀረ-ተባይ</u>

<u>ኬሚካሎች ምዝገባን በተመለከተ፣</u>

51. ማንኛውም በፀረ-ተባይ ኬሚካል በማስመጣት ላይ የተሰማራ ነጋዴ ያልተመዘገበ ፀረ-ተባይ ማምረት፣ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት መሸጥ ወይም መጠቀም አይኖርበትም፡፡

52. በኦዲት ወቅት ወደ ሀገር ውስጥ ምዝገባ ሳይደረግላቸው የገቡ የፀረ-ተባይ ኬሚካል አይነቶችን ለማጣራት በተደረገው ሂደት ውስጥ እ.ኤ.አ ከ2007 እስከ 2009 ድረስ 125 የፀረ-ተባይ ኬሚካል አይነቶች በ19 ድርጅቶች 37563 ኪ.ግ እና 87726 ሊትር ሳይመዘገቡ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

53. ይህንንም በተመለከተ በግብር ሚኒስቴር ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ለአበባ ወይም ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የሚውሉ ፀረ-ተባዮች የምዝገባና የቁጥጥር ሥርዓት ለሌሎች የሚከተሉትን ሥርዓት ሙሉ ለሙሉ ተከትሎ ሥራ ላይ ማዋል ያልተቻለው ልማቱ ግብዓቶቹን ከሚፈለግበት ፍጥነት አንፃር የፍቱንነት ሙከራው ሊጣጣም ባለመቻሉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ሆኖም በወቅቱ ከአዋጅ ውጭ ለምን ያለምዝገባ እንዲገቡ እንደተፈቀደ ለተጠየቁት

ጥያቄ ግን በቂ መልስ አልሰጡም፡፡ በአዲሱ አዋጅ ግን ይህን አስመልክቶ የተሻሻለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

54. በመሆኑም የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል አስፈላጊው ፍተሻ ተደርጐባቸው ሳይመዘገቡ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡና ሥራ ላይ እንዲውሉ መደረጉ ኬሚካሎቹ በሠዎች፣ በእንስሳት፣ በአካባቢ እና በሀገሪቱ የወጭ ግብርና ምርት ንግድ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያስከትል ይችላል፡፡

## የፀረ-ተባይ የፍቱንነት ሙከራ ሪፖርቶች (Efficacy test) ወጥነት ያላቸው መሆኑን በተመለከተ፣

55. የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች የፍቱንነት ሙከራ በሚካሄድበት ወቅት ሪፖርቶች ወጥነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡

56. በኦዲቱ ወቅት በተደረገው የመረጃ ክለሣ በ13/05/02 በአማካሪ ኮሚቴ ቃለ ጉባዔ ላይ በተገለፀው መሠረት በተለያዩ የምርምር ማዕከላትና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በኩል የሚላኩት የፍቱንነት ማረጋገጫ ሙከራ ሪፖርቶች ወጥነት እንደሌላቸው ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

57. የአምቦ የእጽዋት ጥበቃ ምርምር ተቋም ተመራማሪዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የፀረ-ተባይ ኬሚካል የፍቱንነት ሙከራ (efficacy) ለመስራት የተሰጣቸው ውክልና መሆኑን፣ በተቋማት መካከል ቅንጅታዊ አሠራር (coordination) ያለመኖሩ የፍቱንነተ ሙከራ ሪፖርቱ ወጥ ላለመሆኑ ምክንያት እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

58. ይህንንም በተመለከተ በግብርና ሚኒስቴር ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ከላይ የተገለፀው ችግር የመነጨው የፍቱንነት ማረጋገጫ የሚቀርበው ከተለያዩ የምርምር ተቋማት እና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በመሆኑ ችግሩ በአህጉርና በንዑስ ክፍለ አህጉር ደረጃ መፍትሔ እንዲፈለግለት ጥረት እየተደረገ መሆኑን፣ ለጊዜው የመግባቢያ ሰነድ ወይም ፕሮቶኮል አዘጋጅቶ ቢሞከር መፍትሔ ሊሆን እንደሚችል ገልፀዋል፡፡

59. የፍቱንነት ሙከራ ሪፖርቶች ወጥ አለመሆን ፀረ-ተባዮችን አስመልክቶ የሚመጡ ሪፖርቶችን ለመገምገም እና እርምጃ ለመውሰድ አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡

## የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ናሙና ለምዝገባ በሚመጡበት እና ወደ ሀገር ውስጥ በብዛት (Bulk) በሚገቡበት ወቅት ስለትክክለኛነታቸው የላብራቶሪ ፍተሻ መከናወኑን በተመለከተ፣

60. ለምዝገባ የሚመጡ የፀረተባይ ኬሚካል ናሙናዎች እና ከተመዘገቡ በኋላ ጥቅም ላይ እንዲውሉ በብዛት (Bulk) በሚገቡበት ወቅት ስለ ትክክለኛነታቸው የላብራቶሪ ፍተሻ መከናወን እና የፍቱንነት ደረጃቸው አንድ ሊሆን ይገባል፡፡

61. በኦዲቱ ወቅት በተደረገው የመረጃ ክለሣ እና ከሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ ለማረጋገጥ እንደተቻለው የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ወደ ሀገር ውስጥ በብዛት በሚገቡበት ወቅት ናሙና ተወስዶ በቀረበው ናሙና መሠረት የፍቱንነት ደረጃቸው ስለመጠበቁ የላብራቶራ ፍተሻ እንደማይከናወን ነው፡፡ ይህንንም ሥራ ሾላ የሚገኘው በእንስሳት እጽዋት ጤናና ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት የኬሚስትሪ ላብራቶሪ የፀረ-ተባይ ውህድ እና ቅሪት ትንተና (Chemical residue and formulation analysis) በዋናነት የሚያከናውን የነበረ ቢሆንም በአሁኑ ሠዓት ሥራውን ያቋረጠ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

62. ይህንንም በተመለከተ በግብርና ሚኒስቴር ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ከላይ የተገለፀው ችግር እንዳለ አምነው ይህን ለማድረግ የላብራቶሪ አቅም መገንባት ስለሚጠይቅ እና በየኬላዎቹ ላብራቶሪ ማቋቋም ብዙ ገንዘብ የሚጠይቅ፣ ጊዜ እና የሰለጠነ የሰው ኃይል የሚያስፈልግ መሆኑን እንዲሁም ሾላ የሚገኘው ላብራቶሪ ግቢው ለሌላ አገልግሎት እንዲውል እና ላብራቶሪው ደረጃውን በጠበቀ መልኩ በሌላ አካባቢ እንዲደራጅ በመንግስት በመወሰኑ አገልግሎቱ መቋረጡን ገልፀዋል፡፡

63. ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡበት ወቅት በላብራቶሪ ፍተሻ ባለመደረጉ በብዛት ጥቅም ላይ በሚውሉ በተለይም 2,4-D በመሣሠሉ ምርቶች አስመዝጋቢዎች ለምዝገባ የሚያመጡት ናሙና እና ከተመዘገቡ በኋላ በብዛት ገብተው ወደ አርሶ አደሩ ሲደርሱ ፍቱንነታቸው የመቀነስ ሁኔታ እንደሚታይባቸው ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

**የፀረ-ተባይ ኬሚካል መያዣዎች ዳግም**

**ለሌላ ሥራ ጥቅም ላይ እንዳይውሉ**

**ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን በተመለከተ**

64. ማንኛውም የፀረ-ተባይ ኬሚካል መያዣ ዕቃዎች ዳግም ጥቅም ላይ እንዳይውሉ ግብርና ሚኒስቴር ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ተገቢው የግንዛቤ ማስጨበጫ ሊሰጥ ቁጥጥርና ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

65. አገልግሎት የሰጡ የፀረ-ተባይ መያዣዎች ዳግም ጥቅም ላይ እንዳይውሉ የሚያስችል በሀገር አቀፍ ደረጃ የተጠናከረ የቁጥጥር ሥርዓት እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ እንደሌለ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

66. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት የአማራ፣ የኦሮሚያና የደቡብ ሕዝቦች በ7 ዞኖች እና በ18 ወረዳዎች የሚመለከታቸው የግብርና ቢሮ የሥራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለመጠይቅ ጉዳዩ ትኩረት ተሰጥቶት በዕቅድ ተይዞ እንደማይከናወን ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም የኦዲት ቡድኑ በመስክ ሥራ በተዘዋወረበት ወቅት አርሶ አደሮች የተጠቀሙበትን የፀረ-ተባይ መያዣ ለተለያየ አገልግሎት ለዘይት መያዣ፣ ለጨው፣ ለውሀ መጠጫ ለመሣሠሉት ጥቅም ላይ እንደሚያውሉት ለመመልከት ተችሏል፡፡

67. በአለም የምግብ እና የእርሻ ድርጅት መመሪያ መሠረት ጥቅም የሰጡ የፀረ-ተባይ ኬሚካል መያዣዎች ዳግም ለሌላ ሥራ አገልግሎት መስጠት እንደሌለባቸው ያስገነዝባል፡፡ በዚሁም መሠረት የአዳሚ ቱሉ የፀረ-ተባይ ማደራጃ ፋብሪካ ጥቅም የሰጡ የፀረ-ተባይ መያዣ በርሜሎች ዳግም ጥቅም ላይ እንዳይውሉ ቆራርጠው እንደሚያስቀምጡት የኦዲት ቡድኑ በመስክ ጉብኝቱ ወቅት ለመመልከት ችሏል፡፡ ሆኖም የተጠቀሰውን አሠራር ተግባራዊ ለማድረግ በአለም የምግብና የእርሻ ድርጅት ድጋፍ ተገዝቶ በግብርና ሚኒስቴር የፀረ-ተባይ መጋዘን ቅጥር ግቢ ውስጥ ተገጥሞ የነበረው የበርሜል መቆራረጫ (Drum crusher) ኦዲቱ እስከተከናወነበት ወቅት ድረስ ጥቅም ላይ እንዳልዋለ ለማወቅ ተችሏል፡፡

68. ስለጉዳዩ በግብርና ሚኒስቴር የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ በርሜል መቆራረጫው በአለም የምግብ እና የእርሻ ድርጅት በኩል ተገዝቶና በአጠቃቀሙም ላይ ሥልጠና ተሠጥቶ በመጋዘን ውስጥ እንደሚገኝ፣ ማሽኑን ለመጠቀም ያልተቻለበት ምክንያት የአፍሪካ ስቶክ ፓይል ፕሮጀክት የአካባቢና ሶሻል ጥናት ዶክመንት በአለም ባንክ ተቀባይነት እስከሚያገኝና ተጨማሪ የኮንቴይነር ማኔጅመንት ጥናት በማስፈለጉ መሆኑን፣ በአሁኑ ወቅት የአካባቢና ማህበራዊ ጥናቱ በመጠናቀቅ ላይ በመሆኑ እና የኮንቴይነር አስተዳደር ጥናትም በቅርብ ስለሚካሄድ መሣሪያው አገልግሎት መስጠት የሚጀምር መሆኑን ገልፀዋል፡፡

69. ጥቅም የሰጡ የፀረ-ተባይ ኬሚካል መያዣዎች ዳግም ለሌላ አገልግሎት ጥቅም ላይ እንዳይውሉ የሚያስችል የተጠናከረ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ እና የቁጥጥር ሥራ ባለመከናወኑ የሕብረተሰቡ ጤና ለአደጋ ሊጋለጥ እንደሚችል ይታመናል፡፡

<u>**የጤና ጥበቃ ሚኒሰቴር ተወካይ በፀረ-ተባይ**</u>

<u>**አማካሪ ቦርድ ውስጥ መሳተፉን በተመለከተ፣**</u>

70. ስለፀረ-ተባይ ምዝገባና ቁጥጥር በወጣው አዋጅ ቁጥር 674/2002 መሠረት የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ተወካይ በፀረ-ተባይ አማካሪ ቦርድ ውስጥ አባል ሊሆን ይገባል፡፡ ቦርዱም የግብርና ሚኒስትሩን ከፀረ-ተባይ አያያዝና አጠቃቀም አኳያ የሚቀረጹ ብሔራዊ ፖሊሲዎችን፣ ደንቦችን፣ መመሪያዎችንና የአገልግሎት ክፍያዎችን በተመለከተ ማማከር፣ እንዲሁም ፀረ-ተባይን የሚመለከቱ የዓለም ዓቀፍ ስምምነቶችን ከመተግበር አኳያ እና የፀረ-ተባይ ኬሚካል ሥርዓት ውስጥ ማለትም ስለፈቃድ አሰጣጥ፣ የአጠቃቀምና የአወጋገድ ሥርዓትን በተመለከተ በማማከርና በመተባበር መሥራት እንደሚገባው ተገልጿል፡፡

71. ስለጉዳዩ በግብርና ሚኒስቴር የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የጤና ጥበቃ ሚ/ር እስካሁን ያልተሳተፈበትን ምክንያት በግልጽ እንደማያውቁት ገልፀዋል፡፡ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በፀረ-ተባይ አማካሪ ቦርድ ውስጥ ባለመሳተፉ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ተወካይ ከሙያ አንፃር በፀረ-ተባይ አያያዝና አጠቃቀም አኳያ የሚቀረጹ ብሔራዊ ፖሊሲዎችን፣ ደንቦችን፣ መመሪያዎችንና

የአገልግሎት ክፍያዎችን በተመለከተ ለማማከር እንዲሁም ፀረ-ተባይን የሚመለከቱ የዓለም ዓቀፍ ስምምነቶችን ከመተግበር አኳያ እና የፀረ-ተባይ ኬሚካል ሥርዓት ውስጥ ማለትም ስለፈቃድ አሰጣጥ፣ የአጠቃቀምና የአወጋገድ ሥርዓትን በተመለከተ ሊያበረክት ይችል የነበረው አስተዋጽኦ እንዳያበረክት አድርጎታል፡፡

## የፀረ-ተባይ አማካሪ ቦርድ የመግባቢያ ሠነድ መኖሩን በተመለከተ፣

72. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከፀረ-ተባይ አማካሪ ቦርድ አባላት ጋር ተጠያቂነትን የሚያጠናክር እና ለአማካሪ ቦርዱ በአዋጅ የተሠጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችል የመግባቢያ ሰነድ ሊኖረው ይገባል፡፡
73. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከአማካሪ ኮሚቴ አባላት ጋር ማለትም የጤና ጥበቃ ሚ/ር፣ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን፣ የጥራትና ደረጃዎች ባለስልጣን፣ የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣ የብዝሀ ህይወት ጥበቃ ኢንስቲትዩት፣ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ተወካዮች ጋር ተጠያቂነት ሊያጠናክር የሚችል እና ለአማካሪ ኮሚቴው በአዋጅ የተሠጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችል የመግባቢያ ሰነድ እንዳልተፈራረመ በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡
74. ይህንንም በተመለከተ በግብርና ሚኒስቴር ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የመግባቢያ ሠነድ መፈረሙ አስፈላጊነቱ ስላልታየ እና በህግም ይህን እንዲያደርጉ የተደነገገበት ሁኔታ እንደሌለ ገልፀዋል፡፡
75. ሆኖም የፀረ-ተባይ አማካሪ ቦርዱ ከአባላቱ ጋር የመግባቢያ ሠነድ መፈራረሙ የአባላቱን ተጠያቂነትን ሊያጠናክር የሚችልና ለአማካሪ ቦርዱ በአዋጅ የተሠጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችለው እንደሚሆን ይታመናል፡፡

## የተቀናጀ የተባይ መከላከለያ (Integrated Pest Management) በአገር አቀፍ ደረጃ ተጠናክሮ መከናወኑን በተመለከተ፣

76. ፀረ-ተባይ ኬሚካል በአካባቢና በሕብረሰተሰብ ጤና ላይ ሊያደርስ የሚችለው ጉዳት ለመቀነስ እና በአለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው ምርት ከማቅረብ አንፃር የተቀናጀ የተባይ መከላከያ ስልት (Integrated Pest Management) በማስፋፋት የፀረ-ተባይ አጠቃቀም ሊቀነስ ይገባል፡፡
77. የተቀናጀ የተባይ መከላከያ ስልት (Integrated Pest Management) ስነምህዳርን መሠረት ባደረገ ሁኔታ እና በተፈጥሯዊ የመከላከያ ዘዴዎች ሠብልን ከተባይ የመከላከል እና የማልማት ዘዴ ነው፡፡ በአሠራሩም አካባቢንና ተፈጥሮን በመጠበቅ አርሶ አደሮች በዋነኛነት የፀረ-ተባይ ኬሚካል አጠቃቀማቸውን እንዲቀንሱ የሚያስችል እና በውጤቱም ብዛት ያለው የፀረ-ተባይ ኬሚካል

በመጠቀም በሰዎች በእንስሳት እና በአካባቢ ሊደርስ የሚችለውን በጐ ያልሆነ ተጽዕኖ ለመቀነስ ማስቻል ነው፡፡

78. የኦዲት ቡድኑ ተዘዋውሮ በተመለከታቸው በአማራ ክልል የግብርና ቢሮ የሰብል ጥበቃ ቴክኖሎጂ ሽግግር ባለሙያ የተቀናጀ የተባይ መከላከያ ስልትን (Integrated Pest Management) አስመልክቶ ለቀረበላቸው መጠይቅ በሰጡት መልስ የተቀናጀ የተባይ መከላከያ ብዙ ዘርፍ (component) ያለው ቢሆንም ከዛ ውስጥ ግን የተወሠኑ ዘርፎችን (component) በመምረጥ ሊሠራ እንደሚችል ይሁን እንጂ በክልላቸው የተቀናጀ የተባይ መከላከያ ስልትን በአሁኑ ወቅት ተግባራዊ እያደረጉ እንዳልሆነ ገልፀዋል፡፡ በአማራ ክልል የምዕራብ ጐጃም ዞን ግብርና ገጠር ልማት መምሪያ የሥራ ኃላፊ የተቀናጀ የፀረ-ተባይ መከላከል ስልትን አስመልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ የተቀናጀ የተባይ መከላከያ ስልትን የተመለከተ ሥልጠናዎች ከዚህ ቀደም በሲውዲን መንግስ ድጋፍ ይሰጥ እንደነበር አሁን ግን ፕሮግራሙ መቋረጡን፣ በዚህም ምክንያት በዞኑ የተቀናጀ የተባይ መከላከያ ስልት እንደማይሠራበት ገልፀዋል፡፡

79. የኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮ የሥራ ኃላፊ የተቀናጀ የተባይ መከላከያ ስልት ፀረ-ተባይ ኬሚካልን እንደመጨረሻ አማራጭ ከመውሠድ አንፃር ጥቅም እንዳለው ቢታወቅም በክልሉ ተግባራዊ እየተደረገ አለመሆኑን ገልፀዋል፡፡

80. የአምቦ የእጽዋት ጥበቃ ምርምር ማዕከል ባለሙያዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ከግብርና ሚኒስቴር ጋር የተቀናጀ የተባይ መከላከያ ስልትን አስመልክቶ የተጠናከረ ቅንጅታዊ አሠራር እንደሌለ፣ የተቀናጀ የተባይ መከላከያ ስልትን ተግባራዊ ያደረጉ የአበባ እርሻዎች ማለትም ኢቲ ሀይላንድ እና ጆይ ቴክ ውጤታማ መሆናቸውን፣ ነገር ግን አሠራሩን በሌሎች እርሻዎች ላይ ተሞክሮው ያልተስፋፋ በመሆኑ ውጤቱን ለማየት እንዳልተቻለ ገልፀዋል፡፡

81. ስለጉዳዩ በግብርና ሚኒስቴር የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የተቀናጀ የተባይ መከላከያ ስልትን አስመልክቶ ጅምር ሥራ መኖሩን፣ ነገር ግን በቂና አስተማማኝ ነው ማለት እንደማይቻል እና በቀጣይም ቀስ በቀስ ለመተግበር እንደታሰበ ገልፀዋል፡፡

82. የተቀናጀ የተባይ መከላከያ ስልትን አርሶ አደሮች በስፋት እንዲጠቀሙ ባለመደረጉ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች በአካባቢና በሕብረሰተሰቡ ጤና ላይ ሊያደርሱ የሚችሉትን ጉዳት ለመቀነስ እና በአለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው ምርት ከማቅረብ አንፃር ሊገኝ ይችል የነበረውን አስተዋጽኦ ሊቀንሰው እንደሚችል ይገመታል፡፡

**ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ የፀረ-ተባይ ፍላጐት ዳሰሳ ጥናት የሚያከናወን መሆኑን እና ግዢው በዚሁ መሠረት የሚፈፀም መሆኑን በተመለከተ**

83. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የፀረ-ተባይ ፍላጐት ዳሠሣ ጥናት ከየክልሎች በማሰባሰብ ሀገራዊ የፀረ-ተባይ ፍላጐት በማዘጋጀት አስመጪዎች በፍላጐቱ መሠረት ግዥ እንዲያካሂዱ ሊያመቻች ይገባል፡፡

84. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የፀረ-ተባይ ፍላጐት ከየክልሎቹ በየአመቱ የሚያሰባስብ ቢሆንም የተሰበሰቡትን መረጃዎች በማጠናቀር ሀገራዊ የፍላጐት ዳሰሳ ጥናት የማያጠናቅርና አስመጪዎችም ሀገራዊ ፍላጐቱን መሠረት ባደረገ መልኩ እንዲያስመጡ እንደማያደርግ በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

85. ስለጉዳዩ በግብርና ሚኒስቴር የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሀገራዊ የፀረ-ተባይ ፍላጐት ጥናት በማካሄድ በዚሁ መሠረት አስመጪዎች ግዢ እንዲፈጽሙ እንዳላደረጉና ለወደፊቱ ግን ሥራውን ለመሥራት እንደታሰበ ገልፀዋል፡፡

86. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሀገራዊ የፀረ-ተባይ ኬሚካል ዳሰሳ ጥናትን በማካሄድ በዚሁ መሠረት አስመጪዎች እንዲያስገቡ አለማድረጉ ከፍላጐት በላይ የውጭ ግዢ ቢፈፀም በሀገር ደረጃ አላስፈላጊ የፀረ-ተባይ ኬሚካል ክምችት እንዲኖርና እና አገልግሎት ላይ ሳይውሉ የመጠቀሚያ ጊዜው እንዲያልፍ ሊያደርግ ይችላል፡፡ በሌላ መልኩም አስመጪዎች ከፍላጐት በታች ቢያስገቡ ያልተጠበቁ የወረርሽኝ ክስተቶች ቢፈጠሩ አገሪቷን ተጋላጭ ሊያደርጋት ይችላል፡፡

**የፀረ-ተባይ ኬሚካል አጠቃላይ መረጃዎችን ለአጠቃቀም በሚያመች መልኩ በዳታ ቤዝ ሥርዓት መያዙን በተመለከተ**

87. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች አጠቃላይ መረጃዎችን ለአጠቃቀም በሚያመች መልኩ ማለትም ወደ ኢትዮጵያ የገቡ፣ በኢትዮጵያ የተመረቱና ጥቅም ላይ የዋሉ የፀረ-ተባይ ኬሚካል ዓይነቶችንና መጠናቸውን፣ በመንግስትና በግል ይዞታ ሥር ባሉ መጋዘኖች የሚገኙ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን፣ በክምችት ወይም በግብይት ሂደት እያሉ ጥቅም ላይ የማይውሉበት ደረጃ የደረሱ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ለመያዝ የሚያስችል የዳታ ቤዝ ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡

88. በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ እንደተቻለው ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን በሚመለከት በሀገር ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ የፀረ-ተባይ ኬሚካል አይነቶች እና ብዛታቸውን እንዲሁም በመንግስትና በግል ይዞታ ሥር ባሉ መጋዘኖች የሚገኙ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ብዛት እና አይነታቸውን አስመልክቶ ዝርዝር መረጃዎችን በማጠናቀር በዳታ ቤዝ ሥርዓት እንደማይዝ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

89. ስለጉዳዩ በግብርና ሚኒስቴር የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የዳታ ቤዝ ሥርዓት አስፈላጊ መሆኑንና ሥራው በፕሮጀክት ተቀርጾ ተግባራዊ እንደሚደረግ ገልፀዋል፡፡

90. የፀረ-ተባይ ኬሚካል አጠቃላይ መረጃዎች በዳታ ቤዝ ሥርዓት ባለመያዛቸው ወደ ሀገር ውስጥ የገቡት፣ በኢትዮጵያ የተመረቱና ጥቅም ላይ የዋሉ የፀረ-ተባይ ኬሚካል አይነቶችን፣ በመንግስና በግል ይዞታ ሥር ባሉ መጋዘኖች የሚገኙ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን፣ በክምችት ወይም በግብይት ሂደት እያሉ ጥቅም ላይ የማይውሉበት ደረጃ የደረሱትን አስመልክቶ ለውሣኔ አሰጣጥ የሚያስፈልገውን ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት አያስችልም፡፡

**ጥቅም ላይ እንዲውሉ የተመዘገቡና የታገዱ የፀረ-ተባይ**

**ኬሚካሎችን ለህብረተሰቡ በድረ-ገጽና**

**በህትመት ማሳወቅን በተመለከተ**

91. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ተገምግመው የፀደቁ እና የተመዘገቡ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች እንዲሁም በአገር ውስጥ ጥቅም ላይ እንዳይውሉ እገዳ የተጣለባቸውን ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች አስመልክቶ ለህብረተሰቡ በድረ-ገጽና በህትመት በማሠራጨት ለተጠቃሚዎች እንዲደርሱና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

92. በኦዲቱ ወቅት በአማራ፣ በኦሮሚያ እና በደቡብ ክልል በ7 ዞኖች እና በ18 ወረዳ ግብርና ቢሮዎች በተሰበሰበው መረጃ የትኞቹ የፀረ-ተባይ አይነቶች እገዳ የተጣለባቸው የትኞቹ የፀረ-ተባይ አይነቶች ደግሞ አገልግሎት መስጠት እንደሚገባቸው የሚያውቁበት አሰራር እንደሌለ ገልፀዋል፡፡እንዲሁም ከላይ የተጠቀሱት መረጃዎች በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ድረ-ገጽ እንዳልተለቀቀ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

93. ይህንንም በተመለከተ በግብርና ሚኒስቴር ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የተመዘገቡ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ተገልጋዮች ክፍያ ከፍለው መውሰድ እንዳለባቸው ተደንግጐ ስለነበረ ለተጠቀሰው ችግር መንስኤ ሆኖ መቆየቱን፣ ሆኖም በአዲሱ አዋጅ ሕብረተሰቡ መረጃ የማግኘት መብት ስላለው በተለየ ሁኔታ ተዘጋጅቶ እንዲሰጠው ካላስፈለገ በስተቀር በመረጃ መረብ እንዲለቀቅ መደንገጉን፣ ይህም በቅርቡ ተግባራዊ እንደሚደረግ ገልፀዋል፡፡

94. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተመዘገቡ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን እና አገር ውስጥ አገልግሎት እንዳይሰጡ እገዳ የተጣለባቸውን የፀረ-ተባይ ኬሚካል አይነቶች በድህረ-ገጽ እና በህትመት ባለማሳወቁ ሕብረተሰቡ ፍቃድ የተሠጣቸውን ፀረ-ተባይ ኬሚካል አይነቶችን ብቻ ለይቶ በመጠቀም ለአደጋ እንዳይጋለጥ እራሱን ለመከላከል አያስችለውም፡፡

## የፀረ-ተባይ ኬሚካል አጠቃቀምና የግብይት ሥርዓት ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር የተጠናከረ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፣

95. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን አጠቃቀምና ግብይትን በተመለከተ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ማለትም ከክልል ግብርና ቢሮዎች፣ ከፀረ-ተባይ አስመጪ ድርጅቶች እና ፀረ-ተባይን ኬሚካል ከሚጠቀሙ አካላት ጋር የተጠናከረ የመረጃ ልውውጥና የግብረ መልስ ሥርዓት ሊኖረው ይገባል፡፡

96. በኦዲቱ ወቅት መረጃ ከተሰበሰበባቸው የአማራ፣ የኦሮሚያ እና የደቡብ ክልሎች በ7 ዞን በ18 ወረዳ ግብርና ቢሮዎች ግብረ መልስን አስመልክቶ ለግብርና ሚኒስቴር የየአመቱን የፀረ-ተባይ ፍላጐት ከማሳወቅ ውጪ ሌሎች ችግሮችን ማለትም ህገወጥ የፀረ-ተባይ  ኬሚካል ሽያጭን እና ዝውውርን አስመልክቶ የሪፖርቲንግና የግብረ መልስ ሥርዓት ባለመዘርጋቱ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሪፖርት እንደማያደርጉ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

97. ስለጉዳዩ በግብርና ሚኒስቴር የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ መረጃ ለመለዋወጥ የተደራጀ ሥርዓት አለመኖሩን፣ ነገር ግን የተመዘገበ ፀረ-ተባይ ኬሚካል ሲገባ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በኩል ታውቆ እንደሚገባ መረጃ መኖሩን እና የተመዘገቡ ፀረ-ተባዮች ወደፊት በመረጃ መረብ ለመልቀቅ የታሰበ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

98. በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እና በተለያዩ ባለድርሻ አካላት መካከል የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን አጠቃቀምና ግብይትን አስመልክቶ የተጠናከረ የመረጃ ሥርዓት አለመኖሩ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በዘርፉ የሚያጋጥሙ የአሠራር ችግሮችን በአፋጣኝ በመለየት ወቅታዊ የመፍትሔ እርምጃ ለመውሰድና ጠቃሚ የፖሊሲ ሀሣቦችን ለመለየት አያስችለውም፡፡

## ተመዝግበው ጥቅም ላይ የዋሉ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ውጤታማነታቸው የሚገመገም መሆኑን በተመለከተ፣

99. ተመዝግበው ጥቅም ላይ የዋሉ ፀረ-ተባዮች በሁለት ዓመት አንድ ጊዜ  ውጤታማነታቸው ሊገመገም ይገባል፡፡

100. በግብርና ሚኒስቴር የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ብቃት ደረጃ በየጊዜው የሚፈተሽበት (post registration control) አሠራር የሌለ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የመ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ መጠይቅ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

101. ይህንንም በተመለከተ በግብርና ሚኒስቴር ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ በዚህ ረገድ ብዙ ርቀት እንዳልተኬደበት እና በዘንድሮው አንድ ፕሮጀክት ከልማት አጋሮች ጋር በመሆን ተቀርጾ ለመንግስት እንደቀረበና እና ከተፈቀደ በዚህ ዙሪያ የሚሠሩ ሥራዎች ከ2003 በጀት ዓመት ጀምሮ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልፀዋል፡፡ ሆኖም የተመዘገቡ ፀረ-ተባዮች ላይ ቅሬታ

ከቀረበ የሚገመገሙ መሆኑን ነገር ግን የተመዘገበው በሙሉ እንዲገመገም የሚጠይቅ አሠራር የሌለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

102. ተመዝግበው ጥቅም ላይ የዋሉ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች በሁለት ዓመት አንድ ጊዜ ውጤታማነታቸው አለመገምገሙ ሥራ ላይ ከዋሉ በኋላ የሚጠበቀውን ያክል ውጤት ያሰገኙ መሆናቸውን በትክክል ለማረጋገጥ አያስችልም፡፡

## ለሰብልና ለእጽዋት አገልግሎት ላይ መዋል የማይገባቸው አደገኛ ኬሚካሎች በህገ ወጥ መንገድ ጥ ቅም ላይ እንዳይውሉ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ተገቢው ቁጥጥር መደረጉን በተመለከተ

103. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከሚመለከታቸው የክልል መስሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር ለሰብል እና ለእጽዋት አገልግሎት መዋል የማይገባቸውን አደገኛ ኬሚካሎች በህገ-ወጥ መንገድ ጥቅም ላይ እንዳይውሉ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

104. DDT (Dichlorodiphenyltrichloroethane) በአለም አቀፍ ደረጃ በተደረሰው ስምምነት ማለትም (Stockholm convention on persistent organic pollutant) አገልግሎት ላይ መዋል እንደሌለበት ተወስኗል፡፡ በግብርና ምርቶች ላይ ደግሞ በምንም አይነት መልኩ ጥቅም ላይ እንዳይውል ታግዷል፡፡ ኢትዮጵያም ይህንን ስምምነት እ.ኤ.አ በ09/01/2003 ተቀብላ አጽድቃለች፡፡ ይሁን እንጂ አንዳንድ ታዳጊ አገሮች ኢትዮጵያን ጨምሮ ለወባ ትንኝ መከላከያ ጥቅም ላይ እንዲያውሉት ለተወሰነ ጊዜ ተፈቅዷል፡፡

105. የኦዲት ቡድኑ በመስክ ሥራ በተንቀሳቀሰባቸው በአማራ ክልል የባህርዳር ዙሪያ ወረዳ ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት ኃላፊ የDDTን አጠቃቀም አስመልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ በወረዳው ብዛት ያላቸው ጫት አምራች አርሶ አደሮች እንዳሉና DDTን ለተባይ መከላከያነት በጫት ማሳዎች ላይ እንዲሁም በጓያ እና በሽንብራ ላይ እንደሚጠቀሙበት ገልፀዋል፡፡

106. በኦሮሚያ ክልል የምዕራብ ሸዋ ዞን የቶኬ ኮታዬ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት ሥራ ኃላፊ ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ DDT ለበቆሎ እና ለማሽላ ተባይ መከላከያ አርሶ አደሮች በብዛት እንደሚጠቀሙበት ገልፀዋል፡፡ በምዕራብ ሸዋ የአምቦ ወረዳ የግብርና ጽ/ቤት የሰብል ጥበቃ ባለሙያዎች በሰጡት መልስ በገበያ ላይ DDT በስፋት እንደሚሸጥ እና ለበቆሎና ለማሽላ ነቀዝ ማጥፊያ አርሶ አደሮች በስፋት እንደሚጠቀሙበት ገልፀዋል፡፡ በጅማ ዞን የኦሞናዳ ወረዳ የግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት ኃላፊ እና የሰብል ጥበቃ ባለሙያ በሰጡት መልስ ባለፈው 2002 ዓ.ም በቶሌ ሰበታ ቀበሌ ላይ DDT አርሶ አደሮች በርበሬ ላይ ሲረጩ መመልከታቸውን ገልፀዋል፡፡

107. በደቡብ ክልል የግብርና ቢሮ የሰብል ጥበቃ ባለሙያ በሰጡት መልስ DDT በግብርና ሚኒስቴር የተከለከለ ኬሚካል ቢሆንም ምንጩ ባልታወቀ ምክንያት አርሶ አደሮች በእርሻ ላይ በመጠቀማቸው

አንዳንድ የውጭ ንግድ ተቀባይዎች ለምሣሌ ጃፓን የክልሉን ቡና ላለመቀበል ያቆሙበት ወቅት እንደነበር ገልፀዋል፡፡ በጉራጌ ዞን የቀቤና ወረዳ የግብርና ጽ/ቤት ኃላፊ በሰጡት መልስ በወረዳው 23 ቀበሌዎች ሲገኙ 23ቱም ቀበሌዎች ላይ አርሶ አደሮች DDTን በጫት ማሳ ላይ እንደሚረጩ ገልፀዋል፡፡


108. የኦዲት ቡድኑ በአዳማ ከተማ ባደረገው የመስክ ጉብኝት በፀረ-ተባይ መሸጫ ሱቅ ውስጥ የአዳሚ ቱሉ የፀረ-ተባይ ፋብሪካ አርማ ያለበት የDDT ምርቶች በግልጽ ሲሸጥ ተመልክቷል፡፡ ይህ ችግር እንዴት ሊከሰት እንደቻለ የአዳሚ ቱሉ የፀረ-ተባይ ማደራጃ አ.ማ የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ DDTን በተመለከተ ፋብሪካቸው የሚያመርተው ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ትዕዛዝ ሲደርሰው ብቻ መሆኑን፣ ችግሩ ሊከሰት የቻለው ጤና ጥበቃ ተረክቦ በሚያካሂደው የማከፋፈል ሂደት ሊሆን እንደሚችል ገልፀዋል፡፡

109. DDT በህገ ወጥ መንገድ በየሱቁ መሸጡን አስመልክቶ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የቁጥጥር ሥራውን የሚያከናውነው የመድሐኒት አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ስለነበር በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በኩል የቁጥጥር ሥራ እንዳልተሠራ ገልፀዋል፡፡

110. ስለጉዳዩ በመድሐኒት አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ DDT ክልከላ ሲደረግበት ለቁጥጥር እንዲያመች በመጋዘን ያለውን መጠን (stock) እንዲያሳውቋቸው ለየክልል ጤና ቢሮዎች እንዲሁም በግልባጭ ለጤና ጥበቃና ለግብርና ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች መጠየቃቸውን፣ ይሁን እንጂ DDT ክልከላ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ መስሪያ ቤታቸው የቁጥጥር ሥራውን እንዳላካሄደ ገልፀዋል፡፡

111. ይህንንም በተመለከተ በግብርና ሚኒስቴር ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ DDT በግብርና ላይ ጥቅም እንዳይሰጥ ቀደም ሲል በአስተዳደራዊ እርምጃ የተወሰደበት ቢሆንም ነሐሴ/2002 በፀደቀው አዋጅ ተመርኩዞ በሚወጣ ደንብ ይህ በግልጽ መደንገግ እንዳለበት ገልፀዋል፡፡ የተባለው ድርጊት የማይፈለግ ተግባር መሆኑን፣ በሕግ ተደንግጎ ባለመውጣቱ ግን ወደ ሕግ አቅርቦ እርምጃ ለማስወሰድ ክፍተት ሲፈጥር መቆየቱን ገልፀዋል፡፡

112. ለሰብል እና ለእጽዋት አገልግሎት መዋል የማይገባቸውን አደገኛ ኬሚካሎች በህገ-ወጥ መንገድ አርሶ አደሮች ጥቅም ላይ ማዋላቸው በሕብረተሰቡ ጤና፣ በእንስሳት እና በአካባቢ ላይ እጅግ የከፋ አደጋ ሊያስከትል እና አገሪቱ ወደ ውጭ በምትልካቸው የግብርና ምርቶች ገበያ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያስከትል እንደሚችል ይታመናል፡፡




ፎቶ 9 በጤና ጥበቃ ብቻ ጥቅም ላይ መዋል የነበረበት DDT ናዝሬት በየሱቁ እንደሚሸጥ የሚያሳይ ፎቶ

**<u>ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ህገ-ወጥ</u>**

**<u>የፀረ-ተባይ ግብይትን ማስቆምን በተመለከተ፣</u>**

113. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከሚመለከታቸው የክልል መስሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር ፈቃድ ባልተሠጣቸው ህገ-ወጥ ግለሰቦች አማካኝነት የሚካሄደውን የፀረ-ተባይ ኬሚካል ግብይት እንዲቆም ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

114. የኦዲት ቡድኑ በመስክ ሥራ ተዘዋውሮ በተመለከታቸው በደቡብ፣ በአማራ እና በኦሮሚያ ክልሎች በ7 ዞኖች እና በ18 ወረዳዎች ያለው የህገ ወጥ የፀረ-ተባይ ግብይት የቁጥጥር ሥርዓት በተመለከተ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች ተጠይቀው የሚከተሉት ችግሮች መኖራቸውን ገልፀዋል፡፡

115. በደቡብ ክልል ግብር ቢሮ የሰብል ጥበቃ ባለሙያው ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ቀደም ባሉት ጊዜያት ቢሮው ከንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ጋር ለፀረ-ተባይ አከፋፋዮች ወይም ነጋዴዎች በቅንጅት ፈቃድ የሚሰጥበት አሠራር እንደነበር፣ ይሁን እንጂ በአሁኑ ወቅት ግንኙነቱ በመላላቱና ለሥራው ትኩረት ባለመሰጠቱ እንዲሁም የህግ ማዕቀፍ ባለመኖሩ የቁጥጥር ሥራው እንዳልተከናወነ ገልፀዋል፡፡ በጉራጌ ዞን ግብርና መምሪያ የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በህገ-ወጥ

የፀረ-ተባይ ነጋዴዎች ላይ የሚያደርጉት የቁጥጥር ሥራ አለመኖሩንና ይህን ለማስፈፀም የሚያስችል አዋጅ መኖሩን የማያውቁ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

116. በአማራ ክልል የግብርና ቢሮ የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በክልል ደረጃ ያለው አንድ የኢንስፔክሽን ባለሙያ ብቻ በመሆኑና የማስፈፀሚያ አዋጁም በክልል ደረጃ ሥራ ላይ ባለመዋሉ ህገ-ወጦችን በሚፈለገው ደረጃ ለመቆጣጠር እንዳላስቻላቸው ገልፀዋል፡፡ በምዕራብ ጐጃም ዞን ግብር መምሪያ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ቢሮአቸው ከንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ጋር የተጠናከረ ቅንጅታዊ አሰራር ስለሌለው ህገ-ወጥ የፀረ-ተባይ ኬሚካል ነጋዴዎችን ለመከላከል እንዳላስቻላቸው ገልፀዋል፡፡ የባህርዳር ዙሪያ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት ኃላፊ ቁጥጥርን አስመልክቶ በሰጡት መልስ የህግ ከለላ ባለመኖሩ ህገ-ወጥ የፀረ-ተባይ ኬሚካል ነጋዴዎች ላይ የቁጥጥር ሥራ እንደማይሠራ ገልፀዋል፡፡

117. በኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ በክልላቸው ከፍትህ፣ ከፖሊስ እንዲሁም ከንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ጋር ህገ-ወጥ የፀረ-ተባይ ኬሚካል ንግድን ለመከላከል የተጠናከረ ቅንጅታዊ አሠራር እንደሌለ፣ እንዲሁም ፀረ-ተባይን በተመለከተ በፌዴራል ደረጃ የተዘጋጀው አዋጅ መጽደቁን የማያውቁ መሆኑ ገልጸዋል፡፡

118. በጅማ ዞን ግብርና መምሪያ የሰብል ጥበቃ ባለሙያ ጉዳዩን አስመልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ ህገ-ወጥ የፀረ-ተባይ ኬሚካል ንግድን በተመለከተ በዞናቸው የሚሠራ የቁጥጥር ሥራ እንደሌለ፣ የፀረ-ተባይ ኬሚካል ንግድ ፈቃድ ለመስጠት ቀደም ባሉት ጊዜያት ቢሮአቸው ከንግድና ኢንዱስትሪ መምሪያ ጋር በቅንጅት ይሰራ የነበረ ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ ያለ ግብርና መምሪያ እውቅና ለፀረ-ተባይ ኬሚካል ነጋዴዎች የንግድ ፈቃድ እንደሚሰጥ ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም ህገ-ወጦችን ለመቆጣጠር የሚያስችል የማስፈፀሚያ ዝርዝር አዋጅ በክልል ደረጃ ባለመኖሩ ለአሠራር እንዳስቸገራቸው አስረድተዋል፡፡ ለምሣሌ ሊሙ ኮሳ ወረዳ ላይ በህገ ወጥ መንገድ ፀረ-ተባይ ሲሸጡ የተገኙ ግለሰቦችን ፍርድ ቤት ማቅረብ ቢቻልም ፍርድ ቤቱ የመቀጫ አዋጅ አምጡልን በማለቱ አጥፊዎችን ማስቀጣት እንዳልተቻሉ ገልፀዋል፡፡ በዚሁ ዞን የኦሞናዳ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት የሰብል ጥበቃ ባለሙያ በሰጡት መልስ የህግ ማዕቀፍ የሌለ በመሆኑ እና ይህንን ተከታትሎ የሚያስፈጽም የህግ ባለሙያ በግብርና ጽ/ቤት በኩል ያልተደራጀ በመሆኑ ሥራውን ለመሥራት አለመቻሉን እንዲሁም ከንግድና ኢንዱስትሪ፣ ከፍትህ አካላት እና ከፖሊስ ጋር ቅንጅታዊ አሰራር አለመኖሩን ገልፀዋል፡፡

119. የኦዲት ቡድኑ ተዘዋውሮ ባያቸው በአዲስ አበባ ከተማ መርካቶ አካባቢ፣ በባህርዳር፣ ሐዋሳ እና በጅማ ከተሞች በሸቀጣሸቀጥ ሱቆች ውስጥ 2,4D የተባለው የፀረ-አረም ኬሚካል በግልጽ ሲሸጥ ለመመልከት ተችሏል፡፡

120. ስለጉዳዩ በግብርና ሚኒስቴር የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የፌዴራልና የክልል ኃላፊነቶች ተዘርዝረው በሕግ ባልተደነገገበት ሁኔታ ችግሩ እንደነበረ እንደሚታወቅ ገልፀው በአዲሱ ህግ ይህ መፍትሔ እንዲያገኝ በሚቀረጸው ደንብ በማካተት እንዲጸድቅ የሚደረግ መሆኑን፣

ቀደም ባሉት ጊዜያት በመፍትሔነት ውክልና ለክልሎች ተሰጥቶ ቁጥጥሩ እንዲካሄድ ተሞክሮ የነበረ ቢሆንም የተጠበቀውን ያህል ውጤት ባለማምጣቱ በአዲሱ አዋጅ መፍትሔ ሊያገኝ እንደሚችል እንደታሰበ ገልፀዋል፡፡ የሥራ ኃላፊው በክልሎች አዲሱን አዋጅ ማስተዋወቅን አስመልክቶ ሲገልጹ አዋጁ የታተመው ከሁለት ወር በፊት መሆኑን፣ አዋጁ ሲዘጋጅ ከሁለት ዓመት በላይ ምክክር የተደረገበት በመሆኑ እና አሁን የማስተዋወቅ ሥራ ለመሥራት መታቀዱን ገልፀዋል፡፡

121. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከሚመለከታቸው የክልል መ/ቤቶች ጋር በመተባበር ፈቃድ ባልተሠጣቸው ህገ-ወጥ ግለሰቦች አማካኝነት የሚካሄደውን የፀረ-ተባይ ኬሚካል ግብይት እንዲቆም ካላደረገ ችግሩ ተስፋፍቶ በሰዎች በእንስሳትና በአካባቢ ላይ የሚያደርሰው ጉዳት የከፋ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል፡፡




ፎቶ 10 በጅማ ከተማ የሸቀጣሸቀጥ ሱቅ ውስጥ 2-4D ፀረ-ተባይ ኬሚካል እንደሚሸጥ የሚያሳይ ፎቶ



ፎቶ 11 ፀረ-ተባይ ኬሚካል በዱከም ከተማ በግልጽ በገበያ ቦታ እንደሚሸጥ የሚያሳይ ፎቶ



ፎቶ 12 ፀረ-ተባይ ኬሚካል በዱከም ከተማ በግልጽ በገበያ ቦታ እንደሚሸጥ የሚያሳይ ፎቶ

**<u>ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን አስመልክቶ ግንዛቤን የሚያሳድጉ</u>**

**<u>በራሪ ጽሁፎችና የመወያያ መድረኮች ለክልሎችና</u>**

**<u>ለአስመጪዎች በየወቅቱ መዘጋጀቱን በተመለከተ፣</u>**

122. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከክልሎች እና ፀረ-ተባይን ወደ ሀገር ውስጥ ከሚያስገቡ ድርጅቶች ጋር የፀረ-ተባይ ኬሚካል አያያዝና አጠባበቅን በተመለከተ ግንዛቤያቸውን ለማሳደግ የሚረዱ በራሪ ጽሑፎች አዘጋጅቶ እንዲደርሳቸው ሊያደርግ እና ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የመወያያ መድረክ ሊኖረው ይገባል፡፡

123. በኦዲት ወቅት መረጃ የተሰበሰበባቸው የአማራ፣ የኦሮሚያ እና የደቡብ ክልል 7 ዞኖች እና 18 የወረዳ ግብርና ጽ/ቤት የሥራ ኃላፊዎች እንደገለጹት ወረርሽኝ ሲከሰት ብቻ ከግብርና ሚኒስቴር ጋር ከሚደረገው እንቅስቃሴ ውጭ መደበኛ የሆነ የጋራ የውይይት መድረክም ሆነ የፀረ-ተባይ አያያዝና አጠቃቀምን አስመልክቶ ግንዛቤያቸውን የሚያሳድጉበት በራሪ ወረቀቶች እና ጽሑፎች እንደማይደርሷቸው ገልፀዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በናሙና ተመርጠው የታዩ 12 የግል ፀረ-ተባይ ኬሚካል አስመጪዎች ሁሉም ግንዛቤያቸውን የሚያሳድጉበት በራሪ ጽሑፎች፣ ፓምፍሌቶች እንደማይደርሷቸው እና አመታዊ የጋራ የውይይት መድረክም እንደሌለ ገልፀዋል፡፡

124. ይህንንም በተመለከተ በግብርና ሚኒስቴር ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ በቂ ነው ባይባልም በተለያየ መልክ መልዕክቶቻችውን እንደሚያስተላልፉና ግብረ መልስም እንደሚቀበሉ ገልፀዋል፡፡

125. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከክልሎች እና ፀረ-ተባይ ወደ ሀገር ውስጥ ከሚያስገቡ ድርጅቶች ጋር የፀረ-ተባይ አያያዝና አጠባበቅን በተመለከተ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ አለመዘጋጀቱ እና በራሪ ጽሑፎችን በማዘጋጀት እንዲደርሳቸው አለማድረጉ የፀረ ተባይ አያያዝና አጠቃቀምን በተመለከተ ተገቢው ግንዛቤ እንዳይኖራቸው አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ይገመታል፡፡

**<u>ጊዜያቸው ያለፈባቸው (Obsolete) ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ጥቅም</u>**

**<u>ከሚሰጡ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ተለይተው መቀመጣቸውን በተመለከተ</u>**

126. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በፀረ-ተባይ ኬሚካል አስመጪዎች፣ በክልል፣ በዞን እና በወረዳ ግብርና የፀረ-ተባይ ኬሚካል መጋዘኖች ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ጊዜያቸው ካለፈባቸው (obsolete) ኬሚካሎች በተለየ መጋዘን እንዲያስቀምጡ ግንዛቤ ሊፈጥርና ሊከታተል ይገባል፡፡

127. በኦዲት ወቅት በኦሮሚያ ክልል የጅማ ዞን ማና ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት እና በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን የወሊሶ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት የፀረ-ተባይ ኬሚካል መጋዘን ውስጥ ጊዜያቸው ያለፈባቸው 412 ኪ.ግ

ሴቪን (SEVEEN)፣ 1 ኪ.ግ ዳኮሊን (DACOLIN)፣ እና 11 ሊትር 2.4D ጥቅም ከሚሰጡ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ጋር አንድ ላይ ተከማችተው ተገኝተዋል፡፡

128. በደቡብ ክልል የጉራጌ ዞን ቀቤና ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት የፀረ-ተባይ ኬሚካል መጋዘን ውስጥ ጊዜያቸው ያለፈባቸው 40 ኪ.ግ ኮሳይድ (KOSIDE) እና 200 ሊትር ማላታይን (MALATHION) ጥቅም ከሚሰጡ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ጋር አንድ ላይ ተከማችተው ተገኝተዋል፡፡

129. በአማራ ክልል ግብርና ቢሮ እና በምራብ ጎጃም ዞን በደቡብ አቸፈር ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት የፀረ-ተባይ መጋዘን ውስጥ ጊዜያቸው ያለፈባቸው 300 ሊትር 2.4D እና 20 ኪ.ግ ቲራም (TIRAM) እና 36 ሊትር ዲያዞን (DIAZONE 50%) ጥቅም ከሚሰጡ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ጋር አንድ ላይ ተከማችተው ተገኝተዋል፡፡

130. በግብርና ምርት አቅራቢዎች ድርጅት የፀረ-ተባይ ኬሚካል መጋዘን ውስጥ መጠናቸው የማይታወቅ ጊዜያቸው ያለፈባቸው 2.4D, ማላታይን (malathion)፣ አክቴሊክ (Actilic) እና ዳኮሊን (Dacolin) ጥቅም ከሚሰጥ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ጋር አንድ ላይ ተከማችቶ ተገኝቷል፡፡

131. ስለጉዳዩ በግብርና ሚኒስቴር የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ችግሩን ለመፍታት አቅም በፈቀደ መጠን እየሠሩ መሆኑንና ሥራው ወደፊት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ለማስቻል የህግ ማዕቀፍ መሻሻል ስለነበረበት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

132. በፀረ-ተባይ ኬሚካል አስመጪዎች፣ በክልል፣ በዞን እና በወረዳ የግብርና ፀረ-ተባይ ኬሚካል መጋዘኖች ውስጥ ጊዜያቸው ያለፈባቸው ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን አገልግሎት ከሚሰጡ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ጋር በአንድ ላይ መቀመጣቸው አገልግሎት የሚሰጡትን ኬሚካሎች የአገልግሎት ዘመን እንዲያጥር፣ የፍቱንነት ደረጃም እንዲቀንስ ከመደረጉም በላይ በሰው ጤና ላይ ችግር ሊያስከትል እንደሚችል ይታመናል፡፡




ፎቶ *13* ጊዜው ያለፈበት ፀረ-ተባይ ኬሚካል ጥቅም ከሚሰጠው ፀረ-ተባይ ኬሚካል ጋር አብሮ መቀመጡን የሚያሳይ ፎቶ




ፎቶ *14* ጊዜው ያለፈበት ፀረ-ተባይ ኬሚካል ጥቅም ከሚሰጠው ፀረ-ተባይ ኬሚካል ጋር አብሮ መቀመጡን የሚያሳይ ፎቶ

**ለክልል የግብርና ባለሙያዎች ፀረ-ተባይን**

**አስመልክቶ በቂ የግንዛቤ ማስጨበጫ**

**መሰጠቱን በተመለከተ፣**

133. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በክልሎች ለሚገኙ የግብርና ባለሙያዎች እና ለፀረ-ተባይ ኬሚካል ተጠቃሚ አርሶ አደሮች በፀረ-ተባይ አጠባበቅ እና አጠቃቀም ዙሪያ ያላቸውን ግንዛቤ ለማሳደግ የሚረዳ የግንዛቤ ማስጨበጫ የአቅም ግንባታ ድጋፍ ሊሰጥ ይገባል፡፡

134. በኦዲት ወቅት ተዘዋውረን መረጃ በሰበሰብንባቸው በአማራ፣ በደቡብ እና በኦሮሚያ ክልል ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቂ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ሰርቶ አላገኘንም፡፡

135. በአማራ ክልል የግብርና ቢሮ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ከ1999 ዓ.ም በፊት የፀረ-ተባይ መሣሪያ አጠቃቀምን በተመለከተ ከግብርና ሚኒስቴር ባለሙያዎች እየመጡ ስልጠና ይሰጧቸው እንደነበር፣ ሆኖም በአሁኑ ወቅት በወረርሽኝ ዙሪያ የሚሰጥ ሥልጠና ቢኖርም መደበኛ ተባይን አስመልክቶ የሚሰጥ ሥልጠናም ሆነ ድጋፍ የሌለ መሆኑን፣ የግብርና ሚኒስቴር የአቅም ግንባታ ሥራ በየጊዜው ቢሠራ ወቅታዊ እውቀት ስለሚኖር መረጃውን በወቅቱ ለአርሶ አደሩ ከማዳረስ አንፃር ጠቀሜታው ከፍ ያለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በተመሣሣይ መልኩ በሰሜን ጐንደር ዞን የግብርና መምሪያ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ለወረርሽኝ ከሚደረግላቸው የኬሚካል ድጋፍ በስተቀር ፀረ-ተባይን አስመልክቶ የሚደረግላቸው መደበኛ የግንዛቤ ማስጨበጫ ድጋፍ አለመኖሩን ገልፀዋል፡፡

136. የደቡብ ክልል ግብርና ቢሮ የሰብል ጥበቃ ባለሙያ የአቅም ግንባታ ድጋፍን አስመልክቶ በሰጡት መልስ ከፌዴራል ግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ጋር ያላቸው ግንኙነት ዝቅተኛ በመሆኑ ለወረርሽኝ ከሚደረግ ድጋፍ ውጭ ፀረ-ተባይ ኬሚካልን አስመልክቶ የተለየ የአቅም ግንባታ ድጋፍ እንደማይደረግላቸው ገልፀዋል፡፡ የጉራጌ ዞን ግብርና መምሪያ የሰብል ጥበቃ ባለሙያዎች በሰጡት መልስ ከፌዴራል ግብርና ሚኒስቴር በቀጥታ ለዞናቸው የሚደረግ የአቅም ግንባታ ሥራ አለመኖሩን፣ በ1980ዎቹ አካባቢ በክልል ደረጃ አንዴ ስልጠና መስጠቱን ከዚያ ውጭ ግን በሰብል ጥበቃ ዙሪያ ይህ ነው የሚባል ስልጠና አለመሰጠቱን ገልፀዋል፡፡

137. የኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮ የሥራ ኃላፊዎች በሰጡት መልስ ከፌዴራል ግብርና ሚኒስቴር በየአመቱ ስልጠና በቢሮ ደረጃ እንደሚሠጣቸው ሆኖም እነሱ ከአቅም ጋር በተያያዘ ምክንያት ወደ ዞን እና ወረዳ እንዳላደረሱ ገልፀዋል፡፡ የጅማ ዞን ግብርና መምሪያ የሥራ ኃላፊዎች በሰጡት መልስ በፌደራል ግብርና ሚኒስቴር በኩል ወረርሽኝ ሲከሰት ከሚደረግ እንቅስቃሴ ውጭ በቂ የሆነ የአቅም ግንባታ ድጋፍ የማይደረግላቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

138. ስለጉዳዩ በግብርና ሚኒስቴር የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ከመንግስት ከሚፈቅድላቸው በጀት እና ካላቸው አቅም አንፃር ድጋፍ እያደረጉ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

139. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች አያያዝና አጠቃቀምን አስመልክቶ ለሚመለከታቸው የክልል እና የዞን ግብርና ባለሙያዎች በቂ እና ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጫ ድጋፍ አለማድረጉ በፀረ-ተባይ ኬሚካል አጠባበቅ እና አጠቃቀም ላይ ተጠቃሚው በቂ እውቀት እንዳይኖረው በማድረጉ ህብረተሰቡ ለከፋ የጤና ችግር እና የአካባቢ ብክለት እንዲጋለጥ ያደርገዋል፡፡



ፎቶ 15 በዱግዳ ወረዳ አርሶ አደሮች የፀረ-ተባይ መከላከያ ቁሳቁስ ሳይጠቀሙ ፀረ-ተባይ ኬሚካል በማሳቸው ላይ ሲረጩ የሚያሳይ ፎቶ



*ፎቶ 16 በዱግዳ ወረዳ አርሶ አደሮች የፀረ-ተባይ መከላከያ ቁሳቁስ ሳይጠቀሙ ፀረ-ተባይ ኬሚካል ሲያቀናንሱ የሚያሳይ ፎቶ*

## በፀረ-ተባይ ኬሚካል ማከማቻ መጋዘኖች ውስጥ ሌሎች ቁሳቁሶች የማይከማቹ መሆኑን በተመለከተ፣

140. የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን በአግባቡ ለመጠበቅ እና በሰዎች እና በቁሳቁሶች ላይ ሊደርስ የሚችልን የኬሚካል መበከል ለመከላከል በፀረ-ተባይ ኬሚካል ማከማቻ መጋዘኖች ውስጥ ከፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ውጭ ሌሎች ዕቃዎች መከማቸት አይኖርባቸውም፡፡

141. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በተሰበሰቡ መረጃዎች እና በአካል ተገኝተን ባደረግነው ምልከታ በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን ግብርና ቢሮ የፀረ-ተባይ መጋዘን ውስጥ የተለያዩ ዘሮች፣ ሞተር ብስክሌት፣ የውሃ ማጠጪያዎች እና የተለያዩ የቢሮ ቁሣቁሶች ጥቅም ከሚሰጡ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ጋር በአንድ ላይ ተከማችተው ተገኝተዋል፡፡ እንዲሁም በቀርሣ ወረዳ ግብርና ቢሮ የፀረ-ተባይ መጋዘን ውስጥ የንብ ቀፎ፣ ሰም፣ የማር መጭመቂያ እና ማስቀመጫ ቁሣቁሶች በአንድ ላይ ተከማችተው ተገኝተዋል፡፡ በተመሣሣይ መልኩ በኦሞ ናዳ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት የፀረ-ተባይ መጋዘን ውስጥ የንብ ቀፎዎች፣ ሞተር ብስክሌቶች እና የተለያዩ የቢሮ ቁሣቁሶች ጥቅም ከሚሰጡ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ጋር ተከማችተው ተገኝቷል፡፡

142. በደቡብ ክልል ግብርና ቢሮ ማዕከላዊ የፀረ-ተባይ ኬሚካል መጋዘን ውስጥ ማዳበሪያዎች፣ የመርጫ መሣሪያዎች የተለያዩ ቁሣቁሶች ጥቅም ከሚሰጡ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ጋር አብረው ተከማችተው ተገኝተዋል፡፡ በጉራጌ ዞን በአበሽጌ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት የፀረ-ተባይ ኬሚካል መጋዘን ውስጥ ደግሞ ምርጥ ዘር፣ ማዳበሪያ እና የተለያዩ ቁሣቁሶች ጥቅም ከሚሰጡ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ጋር ተከማችተው ተገኝተዋል፡፡

143. በአማራ ክልል የሰሜን ጐንደር ዞን ግብርና መምሪያ የፀረ-ተባይ ኬሚካል መጋዘን ውስጥ የምግብ ዘይት ጀሪካኖች እና የተለያዩ ቁሣቁሶች ጥቅም ከሚሰጡ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ጋር አንድ ላይ ተከማችተው ተገኝተዋል፡፡ እንዲሁም በባህርዳር ዙሪያ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት የፀረ-ተባይ መጋዘን ውስጥ የውሀ መሣቢያ ሞተሮች፣ የሞተር መለዋወጫዎች፣ የተለያዩ ጐማዎች፣ የንብ ቀፎዎች፣ ማዳበሪያ እና የተለያዩ ቁሣቁሶች ጥቅም ከሚሰጡ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ጋር ተከማችተው ተገኝተዋል፡፡

144. ከዚህ በተጨማሪ በናሙና ተመርጠው በኦዲት ወቅት ከታዩት የግል የፀረ-ተባይ ኬሚካል አስመጪዎች ውስጥ በላየንስ ኢንተርናሽናል የፀረ-ተባይ አስመጪ ድርጅት የፀረ-ተባይ ኬሚካል መጋዘን ውስጥ ወደ 120 ኩንታል ጤፍና ስንዴ ጥቅም ከሚሰጡ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ጋር ተከማችቶ ተገኝቷል፡፡ይህንንም በተመለከተ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የድርጅቱ የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ጤፍና ስንዴውን ከፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ጋር በአንድ መጋዘን ውስጥ ያስቀመጡት የከፋ ችግር ያመጣል የሚል ግምት ስለሌላቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም በአግሪ ሼር የፀረ-ተባይ አስመጪ ድርጅት የፀረ-ተባይ ኬሚካል መጋዘን ውስጥ ማዳበሪያ ከፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ጋር በአንድ

ላይ ተከማችቶ ተገኝቷል፡፡ በቡና ተክል ልማት ድርጅት የሊሙ ኮሣ እርሻ ድርጅት የፀረ-ተባይ ኬሚካል መጋዘን ውስጥ ደግሞ ማዳበሪያ እና በግምት ወደ10000 የሚጠጉ  የተበከሉ የኬሚካል ጀሪካኖች ከፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ጋር አብረው ተከማችተው ተገኝተዋል፡፡

145. ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች ለምን ሊከሰቱ እንደሚችሉ የሚመለከታቸው የክልል፣ የዞን እና የወረዳ ግብርና የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው ለየቢሮዎቹ የተለያዩ ቁሣቁሶች ማስቀመጫ የሚሆን እራሱን የቻለ መጋዘን ለመገንባት የበጀት እጥረት በመኖሩ ምክንያት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

146. ስለጉዳዩ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የንብ ቀፎዎች እና የምግብ ነክ ቁሣቁሶች ከፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ጋር በአንድ ላይ ማከማቸት እጅግ ጉጂ እና አደገኛ መሆኑን አመልክተው ለወደፊቱ መስተካከል እንደሚኖርበት ገልፀዋል፡፡

147. በፀረ-ተባይ ኬሚካል መጋዘኖች ውስጥ ከፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ጋር ምግብ ነክ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሣቁሶች በአንድ ላይ መቀመጣቸው በሰዎች ጤንነት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል፡፡ እንዲሁም በፀረ-ተባይ ኬሚካል መጋዘኖች ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ የፀረ-ተባይ ፍሰቶች ቢያጋጥሙ በአፋጣኝ ለማጽዳት እና ከአደጋ ለመከላከል አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡




ፎቶ 17 ፀረ-ተባይ ኬሚካል ከማዳበሪያ ጋር አብሮ መቀመጡን የሚያሳይ ፎቶ




ፎቶ 18 ፀረ-ተባይ ኬሚካል ከሌሎች ቁሣቁሶች ጋር አብሮ መቀመጣቸውን የሚያሳይ ፎቶ




ፎቶ 19 ፀረ-ተባይ ኬሚካል ከምርጥ ዘር ጋር አብሮ መቀመጣቸውን የሚያሳይ ፎቶ




ፎቶ 20 በጨርቅ በተከፈለ አንድ መጋዘን ውስጥ ፀረ-ተባይ ኬሚካል ከእህል ጋር መቀመጡን የሚያሳይ ፎቶ




ፎቶ 21 በፀረ-ተባይ ኬሚካል መጋዘን ውስጥ የንብ ቀፎ መቀመጡን የሚያሳይ ፎቶ

## ጊዜ ያለፈባቸው ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች እና በፀረ-ተባይ ኬሚካል የተበከሉ ቁሣቁሶች ለሰውና ለአካባቢ ጉዳት በማያደርስ መልኩ መጠበቃቸውን በተመለከተ፣

148. ጊዜ ያለፈባቸው ፀረ-ተባዮች እና በፀረ-ተባይ የተበከሉ ቁሣቁሶች በጥንቃቄ ታሽገው በሰውና በአካባቢ ላይ ጉዳት በማያደርስ መልኩ ሊከማቹና ሊጠበቁ ይገባል፡፡

149. በኦዲት ወቅት ከተሰበሰበው መረጃ እና በአካል ተገኝተን ባደረግነው ምልከታ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የፀረ-ተባይ ኬሚካል ማከማቻ መጋዘን ውስጥ ጊዜው ያለፈበት 9767 ሊትር ማላታይን እና 200 ኪ.ግ የሚጠጋ DDT ደረጃውን ባልጠበቀና ሊወድቅ በደረሰ ቤት ውስጥ ተከማችቶ ተገኝቷል፡፡

150. በዚህ የፀረ-ተባይ ኬሚካል ማከማቻ መጋዘን አካባቢ በአቅራቢያው በአማካኝ አራት አራት የቤተሠብ አባላት ያሉአቸው፣ 5 አባ ወራዎች የሚኖሩ መሆኑን፣ ሽታውም በአካባቢው ነዋሪዎች ላይ ከፍተኛ ችግር እያደረሰባቸው መሆኑን፣ ይህ ችግር እንዲቀረፍላቸው ለተለያዩ የመንግስት አካላት ጥያቄ ቢያቀርቡም እስካሁን መፍትሔ እንዳላገኙ ነዋሪዎቹ ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም ይህ ችግር በአቅራቢያው በሚገኘው ተስፋ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመማር ማስተማር ሂደት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ እንዳስከተለ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ስለጉዳዩ የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ የፀረ-ተባይ ኬሚካሉ መጥፎ ሽታ የተማሪዎችንና የመምህራንን ጤንነት በከፍተኛ ሁኔታ እየጐዳ በመምጣቱ አብዛኛዎቹ በመተንፈሻ አካላት በሽታ እየተጐዱ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ የተማሪዎች ቁጥር ከአመት ወደ አመት እየቀነሰ መምጣቱን እንዲሁም መምህራን በከፍተኛ ሁኔታ በየጊዜው ሥራ በመልቀቃቸው መቸገራቸውን ገልፀዋል፡፡

151. የኦዲት ቡድኑ በትምህርት ቤቱ በተገኘበት ወቅት የት/ቤቱን የተማሪዎችን ቅበላ የ12 ዓመት መረጃ በማየት የተማሪዎች ቁጥር ከ1991 ዓ.ም ከነበረበት ከ1001 በ2002 ዓ.ም ቁጥሩ ወደ 551 ማሽቆልቆሉን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ለዚህም ችግር ዋነኛው ምክንያት ለ11 ዓመት ያህል የተከማቸው የፀረ-ተባይ ኬሚካል ያስከተለው ችግር መሆኑን የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ገልፀዋል፡፡

152. በኦሮሚያ ክልል በምስሥራ ሸዋ ዞን የዱግዳ ወረዳ የግብርና ጽ/ቤት ቢሮ እና የፀረ-ተባይ ኬሚካል መጋዘን በአንድ ህንፃ ውስጥ የሚገኝ መሆኑን፣ ጊዜያቸው ያለፈባቸው ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ከተለያዩ ቁሣቁሶች ጋር በመጋዘኑ ውስጥ አብረው መከማቸታቸው ሽታው የቢሮ ሠራተኞችን ጤንነት እያወከ እንደሚገኝ ለመመልከት ተችሏል፡፡ እንዲሁም በደቡብ ክልል በአበሽጌ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት የፀረ-ተባይ መጋዘን ውስጥ ጊዜያቸው ያለፈባቸው ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ጥቅም ከሚሰጡ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች እና ከተለያዩ ቁሣቁሶች ጋር ጥንቃቄ በጐደለው መልኩ አንድ ላይ መቀመጣቸውን ለመመልከት ተችሏል፡፡

153. ከዚህ በተጨማሪ በግብርና ሚኒስቴር የፀረ-ተባይ ኬሚካል ማከማቻ መጋዘን ቅጥር ጊቢ ውስጥ የሚገኙ አገልግሎት የማይሰጡ የፀረ-ተባይ መርጫ መሣሪያዎች እና የተለያዩ ቁሣቁሶች ከፀረ-ተባይ ኬሚካል መጋዘኑ ጀርባ ሜዳ ላይ ተከማችተው እንደሚገኙ ለመመልከት ተችሏል፡፡

154. ስለጉዳዩ በግብርና ሚኒስቴር የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በኩል የተከማቸውን 9767 ሊትር ማላታይንና 200 ኪ.ግ የሚጠጋ DDTን አስመልክቶ በመጀመሪያ በተካሄደ የማስወገድ ሁለት ዙሮች ባለቤቱ ባለማሳወቁ (በሕግ ክርክር ስለነበረ) ያልተወገደ መሆኑንና ከዚያ በኋላ ደግሞ ዓለም አቀፍ አሠራሩን መሠረት ካላደረገ የማይሠራ በመሆኑ ገንዘብ ከተገኘ በኋላም ከሁለት ዓመት በላይ ሳይወገድ መዘግየቱን ገልፀዋል፡፡

155. ከላይ በዝርዝር በተገለፀው መልኩ ጊዜ ያለፈባቸው ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች እና በፀረ-ተባይ ኬሚካል የተበከሉ ቁሣቁሶች በጥንቃቄ ታሽገው በሰውና በአካባቢ ላይ ጉዳት በማያደርስ መልኩ ባለመቀመጣቸው በአካባቢው ህብረተሰብ ጤንነት እና በመማር ማስተማሩ የሥራ ሂደት ላይ ጉዳት እያስከተሉ እንደሚገኙ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡




ፎቶ 22 በፀረ-ተባይ የተበከሉ የተለያዩ እቃዎች ደረጃውን ባልጠበቀ ቦታ ወይም በሜዳ ላይ የተከማቹ መሆኑን የሚያሳይ ፎቶ




ፎቶ 23 በርካታ ቁጥር ያላቸው የፀረ-ተባይ መያዣ ዕቃዎች ደረጃውን ባልጠበቀ ቦታ ተከማችተው የሚያሳይ ፎቶ




ፎቶ 24 በርካታ ቁጥር ያላቸው የፀረ-ተባይ መያዣ ዕቃዎች ደረጃውን ባልጠበቀ ቦታ ተከማችተው የሚያሳይ ፎቶ




ፎቶ 25 በርካታ ቁጥር ያላቸው የፀረ-ተባይ መያዣ ዕቃዎች ደረጃውን ባልጠበቀ ቦታ ተከማችተው የሚያሳይ ፎቶ

**ጊዜ ያለፈባቸውን የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ለማሰባሰብ፣ ለማጓጓዝና ለማስወገድ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሠራ መሆኑን በተመለከተ፣**

156. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጊዜያቸው ያለፈባቸውን ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች በማሰባሰብ፣ በማከማቸትና በማጓጓዝ ሥራ ላይ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በማሣተፍ በቅንጅት ሊሠራ ይገባል፡፡
157. በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች እና ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለመረዳት እንደተቻለው በኢትዮጵያ ጊዜያቸው ያለፈባቸውን ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ለማስወገድ እ.ኤ.አ ከ2003 ጀምሮ ሁለት ፕሮጀክቶች ተቀርፀው ዓለም አቀፍ መስፈርቶችን ባሟላና የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን፣ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የአለም የምግብና እርሻ ድርጅት እንዲሁም የዩኤስ አሜሪካን መንግስት፣ የቤልጅዬምን መንግስት፣ የጃፓንን መንግስት፣ የስውዲንን መንግስት፣ የኔዘርላንድን መንግስት ፣ የፊንላንድን መንግስት እና የፀረ-ተባይ አምራች ማህበራትን በማሳተፍ መጠኑ 2200 ቶን የሚሆን ጊዜያቸው ያለፈባቸው ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች እንደተወገዱ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በአፍሪካ ስቶክ ፓይልስ ፕሮጀክት 400 ቶን የሚሆኑ ጊዜያቸው ያለፈባቸው ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ለማስወገድ በዝግጅት ላይ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

158. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጊዜያቸው ያለፈባቸውን ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች እንዲወገዱ ፕሮጀክቶችን በመቅረጽና የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ ያከናወነው ሥራ ውጤታማ እንደነበር ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

**ጊዜያቸው ያለፈባቸው ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ለመከላከልና ለማስወገድ በሁለተኛው ዙር በዕቅድ የተያዘው ገንዘብ ሥራ ላይ መዋሉን በተመለከተ፣**

159. በተለያዩ ጊዜያቶች ጊዜያቸው ያለፈባቸው ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ለማስወገድ የተቋቋሙ ፕሮጀክቶች የተመደበላቸውን በጀት ባግባቡና በብቃት ሊጠቀሙ ይገባል፡፡

160. በኦዲቱ ወቅት በተደረገ የመረጃ ክለሣ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጊዜያቸው ያለፈባቸውን ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች በማስወገድ ሂደት ውስጥ ፕሮጀክት ቀርጾ ሥራውንም እያከናወነም እንደሚገኝ ይታወቃል፡፡ በዚሁ መሠረት በሁለተኛው ዙር ጊዜያቸው ያለፈባቸውን ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች በመከላከል እና ለማስወገድ እ.ኤ.አ በ24 ኤፕሪል 2003 ፕሮጀክት ቀርጾ ከቤልጂየም መንግስት ጋር ከተፈራረመው $4,070,000 (አራት ሚሊዮን ሰባ ሺ ዶላር) ውስጥ በወቅቱ ጥቅም ላይ ሳይውል የቀረ ብር 1,211,405.00 (አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ አስራ አንድ ሺህ አራት መቶ አምስት ብር) ለቤልጂየም መንግስት ተመላሽ ማድረጉ ታውቋል፡፡

161. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የግብርና ሚኒስቴር የሥራ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ፕሮጀክቱ ሲቀረጽ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውሰጥ ጥቅም ላይ ያልዋለ ገንዘብ ለለጋሹ እንደሚመለስ በፕሮጀክት ሰነዱ የሰፈረ ስለነበረ በዚህ አግባብ የተመለሰ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ለመዘግየቱ ደግሞ የቤልጂየም መንግስት ለኢትዮጵያ መንግስት የሚያደርገው የልማት ድጋፍ በፖሊሲ ለውጥ ምክንያት ሊቀጥልበት ባለመቻሉ በተፈጠረ ክፍተትና በኢትዮጵያ ወገንም በፕሮጀክት መጀመሪያ ወቅት የተከሰቱ የመዘግየት ሁኔታዎች በመፈጠራቸው ቢሆንም ፕሮጀክቱን በበላይነት የሚመራው አስተባባሪ ኮሚቴ (Steering committee) የፕሮጀክቱ ዕድሜ እንዲራዘም ጠይቆ ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ ጥቅም ላይ እንዲውል በማድረግ የተረፈው ገንዘብ የተመለሰ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

162. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፕሮጀክት ቀርጾ ለማስፈፀሚያ የሚያገኘውን ገንዘብ በወቅቱ ሥራ ላይ እንዲውል ከፍተኛ ጥረት ካላደረገ የተገኘው ገንዘብ ለታቀደለት ዓላማ ሳይውል እና ችግሩም ሳይቃለል ገንዘቡ የሚመለስበት ሁኔታ ሊከሰት ይችላል፡፡

# ክፍል ሦስት

## መደምደሚያ

- በናሙና ተመረጠዉ ከታዩት የተላያዩ የፀረ-ተባይ ኬሚካል አስመጪ ድርጅቶች እና በኦሮሚያ፣ በአማራና በደቡብ ክልሎች በሚገኙ የዞንና የወረዳ ግብርና ቢሮዎች የፀረ-ተባይ መጋዘኖች መመሪያዉ የሚጠይቀዉን መስፈርት ሙሉ በሙሉ ባሟላ መልኩ አለመገንባታቸዉ፣
- የፀረ-ተባይ ኬሚካል ማከማቻ መጋዘኖች ከመስራታቸው በፊት የስጋት ትንተና ባለመሰራቱ በናሙና ተመረጠው የታዩት የፀረ-ተባይ መጋዘኖች አብዛኞቹ ሠዎችና እንስሳት በሚገኝበት አካባቢ መገንባታቸዉ ፣
- በናሙና ተመርጠው የታዩ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች አስመጪ ድርጅቶችና የፀረ-ተባይ ተጠቃሚዎች አብዛኞቹ ለሠራተኞቻቸው የመከላከያ ልብስ፣ ጫማዎች፣ ጓንት እና የመተንፈሻ አካላት መሸፈኛ ቁሳቁሶችን አለማሟላታቸዉ፣
- የፀረ-ተባይ ኬሚካል መያዣዎች በአብዛኛው በበርሜል የሚዘጋጁ፣ ለአጠቃቀም አመቺ ያልሆኑ እና የማቀናነሻ መሣሪያዎች ባልተሟሉባቸው አካባቢዎች የፀረ-ተባይ ኬሚካሉን በሚያከፋፍሉ በአንዳንድ የክልል፣ የዞን እና የወረዳ ሠራተኞች ላይ የጤና ጉዳት ማስከተላቸው፣
- በናሙና ተመርጠው በታዩ የአበባ ፀረ-ተባይ ኬሚካል አስመጪ ድርጅቶች በፀረ-ተባይ ኬሚካል መያዣ እቃዎች ላይ መለያውን (labeling) በግልጽ የፀረ-ተባይ ኬሚካሉን የወል መጠሪያ እና የድብልቅ መጠን፣ የአጠቃቀም መመሪያ፣ ፀረ-ተባዩ ጥቅም ላይ ከዋለ በኋላ አደጋ እንዳያስከትል መቆየት የሚያስፈልግበት ጊዜ፣ የአለም የጤና ጥበቃ ድርጅት በወሰነው ምደባ መሠረት አደገኛነቱን የሚያስጠነቅቅ የጽሑፍና ስዕላዊ መግለጫ፣ በአደጋ ጊዜ ሊወሰድ የሚገባው የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ አሠጣጥን በተመለከተ፣ የተመረተበት ቀን እና የአገልግሎት እድሜው በግልጽ በአማርኛና በእንግሊዝኛ የማይለጥፉ መሆናቸው፣
- ለአበባ እርሻዎች የሚያገለግሉ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል አስፈላጊው ፍተሻ ተደርጐባቸው ሳይመዘገቡ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡና ሥራ ላይ እንዲውሉ መደረጉ፣
- በተለያዩ የምርምር ማዕከላትና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በኩል የሚላኩት የፍቱንነት ማረጋገጫ ሙከራዎች (Efficacy test) ሪፖርቶች ወጥነት የሌላቸው መሆኑ፣
- ለምዝገባ የሚመጡ የፀረተባይ ኬሚካል ናሙናዎች እና ከተመዘገቡ በኋላ ጥቅም ላይ እንዲውሉ በብዛት (Bulk) በሚገቡበት ወቅት የፍቱንነት ደረጃቸው ተመሣሣይ መሆናቸው ለማረጋገጥ የላብራቶሪ ፍተሻ የማይከናወን መሆኑ፡፡
- ጥቅም የሰጡ የፀረ-ተባይ ኬሚካል መያዣዎች ዳግም ለሌላ አገልግሎት ውለው የሕብረተሰቡን ጤና ለአደጋ እዳያጋልጡ የተጠናከረ የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የቁጥጥር ሥራ አለመከናወኑ፣
- የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በፀረ-ተባይ ኬሚካል አማካሪ ቦርድ ውስጥ እሰካሁን በአባልነት አለመሳተፉ፣

- የግብርና ሚኒስቴር ከፀረ-ተባይ አማካሪ ቦርድ አባላት ጋር ተጠያቂነትን የሚያጠናክር እና ለአማካሪ ቦርዱ በአዋጅ የተሠጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችል የመግባቢያ ሰነድ አለመፈራረሙ፣
- ፀረ-ተባይ ኬሚካል በአካባቢና በሕብረሰተሰብ ጤና ላይ ሊያደርስ የሚችለው ጉዳት ለመቀነስ እና በአለም አቀፍ ገበያ ተቀባይነት ያለው ምርት ከማቅረብ አንፃር የተቀናጀ የተባይ መከላከያ ስልት (Integrated Pest Management) በለመስፋፋቱ የፀረ-ተባይ አጠቃቀምን ለመቀነስ አለማቻሉ፣
- የግብርና ሚኒስቴር ከየክልሎች የፀረ-ተባይ ፍላጐት በማሰባሰብ ሀገራዊ የፀረ-ተባይ ፍላጐት አለማዘጋጀቱና አገራዊ ፍላጎትን መሰረት ባደረገ መልኩ አስመጪዎች የውጭ ግዢ እንዲፈጸሙ አለማድረጉ፣
- የግብርና ሚኒስቴር የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች አጠቃላይ መረጃዎችን ለአጠቃቀም በሚያመች መልኩ ማለትም ወደ ኢትዮጵያ የገቡ፣ በኢትዮጵያ የተመረቱና ጥቅም ላይ የዋሉ የፀረ-ተባይ ዓይነቶችንና መጠናቸውን፣ በመንግስትና በግል ይዞታ ሥር ባሉ መጋዘኖች የሚገኙ ፀረ-ተባዮችን፣ በክምችት ወይም በግብይት ሂደት እያሉ ጥቅም ላይ የማይውሉበት ደረጃ የደረሱ ፀረ-ተባዮችን መረጃ ለመያዝ የሚያስችል የዳታ ቤዝ ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ አለማድረጉ፣
- የግብርና ሚኒስቴር ተገምግመው የፀደቁ እና የተመዘገቡ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች እንዲሁም በአገር ውስጥ ጥቅም ላይ እንዳይውሉ እገዳ የተጣለባቸውን ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች አስመልክቶ ለህብረተሰቡ በድረ-ገጽ አለማሠራጨቱና በህትመት በማዘጋጀት ለተጠቃሚዎች እንዲደርሱና ጥቅም ላይ እንዲውሉ አለማድረጉ፣
- የግብርና ሚኒስቴር እና በተለያዩ ባለድርሻ አካላት መካከል የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን አጠቃቀምና ግብይትን አስመልክቶ የተጠናከረ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት አለመኖሩ፣
- ተመዝግበው ጥቅም ላይ የዋሉ ፀረ-ተባዮች በየጊዜው ውጤታማነታቸው ባለመገምገሙ ሥራ ላይ እየዋሉ ያሉት የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች የሚጠበቀውን ያክል ውጤት እያስገኙ መሆናቸው በትክክል ለማወቅ አለመቻሉ፣
- የግብርና ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው የክልል መ/ቤቶች ጋር በመተባበር ለሰብል እና ለእጽዋት የተባይ መከላከያ አገልግሎት ላይ መዋል የማይገባቸውን አደገኛ ኬሚካሎች በህገ-ወጥ መንገድ ጥቅም ላይ እንዳይውሉ አሰፈላጊውን ቁጥጥርና ክትትል አለማድረጉ፣
- የግብርና ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው የክልል መ/ቤቶች ጋር በመተባበር ፈቃድ ባልተሠጣቸው ህገ-ወጥ ግለሰቦች አማካኝነት የሚካሄደውን የፀረ-ተባይ ኬሚካል ግብይት እንዲቆም ክትትል አለማድረጉ፣
- የግብርና ሚኒስቴር ከክልሎች እና ፀረ-ተባይን ወደ ሀገር ውስጥ ከሚያስገቡ ድርጅቶች ጋር የፀረ-ተባይ አያያዝና አጠባበቅን በተመለከተ ግንዛቤያቸውን ለማሳደግ የሚያስችሉ አመታዊ የውይይት መድረክ አለማዘጋጀቱ እና በራሪ ጽሑፎችን እንዲደርሳቸው አለማድረጉ፣

- የግብርና ሚኒስቴር በፀረ-ተባይ አስመጪዎች እና በክልል፣ በዞን እና በወረዳ ግብርና የፀረ-ተባይ መጋዘኖች ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ጊዜያቸው ካለፈባቸው የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች በተለየ መጋዘን እንዲያስቀምጡ ክትትል አለማድረጉ፣
- የግብርና ሚኒስቴር የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች አያያዝና አጠቃቀምን አስመልክቶ ለሚመለከታቸው የክልል እና የዞን ግብርና ባለሙያዎች በቂ እና ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጫ ድጋፍ አለማድረጉ፣
- በኦዲት ወቅት በታዩት በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኘው የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የፀረ-ተባይ መጋዘን፣ በኦሮሚያ፤ በአማራ እና በደቡብ ክልል ግብርና ቢሮ በፀረ-ተባይ ኬሚካል መጋዘኖች ውስጥ ከፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ጋር ምግብ ነክ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሣቁሶች በአንድ ላይ ተቀምጠው መገኘታቸው፣
- በኦዲት ወቅት በታዩት በኦሮሚያ፤ በአማራ እና በደቡብ ክልል ግብርና ቢሮ ጊዜ ያለፈባቸው ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች እና በፀረ-ተባይ ኬሚካል የተበከሉ ቁሣቁሶች በጥንቃቄ ታሽገው በሰውና በአካባቢ ላይ ጉዳት በማያደርስ መልኩ አለመጠበቃቸው፣

በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

ይህም የሚያሳየው የፀረ-ተባይ አስመጪ ድርጅቶች፣ የክልልና የዞን የግብርና ቢሮዎች፣ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና የግብርና ሚኒስቴር በፀረ-ተባይ አጠባበቅና አጠቃቀምን በተመለከተ የሚፈለግባቸውን ያህል ያልሰሩ መሆኑን ነው፡፡ ይህም አሠራር በህብረተሰቡ ጤና እና በአካባቢው ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትል መሆኑ ይታመናል፡፡ ስለሆነም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች ለማሻሻል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሐሣቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኙ ግኝቶችን በተመለከተ ከግብርና ሚኒስቴር ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተካሄደው የመውጫ ስብሰባ ውይይት በኦዲቱ ወቅት የተገኙ ግኝቶችን ትክክለኛ መሆናቸውን እና ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተቀበላቸው መሆኑን ገልጸው የሚከተሉት አስተያየቶች ግን በሪፖርቱ ትኩረት እንዲያገኙ ኃሳብ አቅርበዋል፡፡

- ከፀረ ተባይ አያያዝ እስከ አወጋገድ ድረስ ቀደም ባሉት ጊዜያት የሕግ ክፍተት ስለነበረ በአሰራር ላይ ችግር ሲፈጥር መቆየቱንና በአሁኑ ወቅት ግን የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የስራ ኃላፊነትን በግልጽ ያስቀመጠ የፀረ ተባይ ኬሚካል አዋጅ በመውጣቱ ለወደፊቱ በኦዲት የተገለጹ ችግሮችን ለመፍታት ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ፣
- የግብርና ሚኒስቴር የአሠራር ስርዓት ማሻሻያ BPR አጥንቶ ወደ ተግባር የገባ በመሆኑ በኦዲቱ ተለይተው የቀረቡት ግኝቶች እንደ ትልቅ ግብዓት እንደሚያገለግሉና በBPR ጥናቱ መሠረት በተለይ

ፀረ ተባይ ኬሚካልን በተመለከተ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር የተጠናከረ ግንኙነት በመፍጠር የሚሠራ መሆኑን፣

- የፀረ ተባይ ኬሚካል አያያዝና አጠባበቅን በተመለከተ ለክልሎች በተቻለ መጠን ወደፊት ድጋፍ የሚደረግ መሆኑን፣
- ህገወጥ የፀረ ተባይ ንግድን ለማስቆምና አርሶ አደሩ እንደ DDT ያሉትን አደገኛ ፀረ ተባዮችን እንዳይጠቀም ጠንካራ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ የሚሠራ መሆኑን፣
- የተቀናጀ የተባይ መከላከያ ስርዓት (IPM) በተመለከተ በግብርና ሚኒስቴር ደረጃ በዕቅድ የተያዘ በመሆኑ ለወደፊቱ በሠፊው የሚሠራበት መሆኑን፣
- ሳይመዘገቡ ወደ ሀገር ውስጥ ይገቡ የነበሩት የአበባ እርሻ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች በተመለከተ ዘርፉ ለሀገራችን አዲስ ስለነበር በቂ ዝግጅት ያልነበረ በመሆኑ በልዩ ሁኔታ አስመጪዎች እያስገቡ ሲሰራበት የቆየ ቢሆንም ለወደፊቱ ግን ወደ ምዝገባ ስርዓት መግባት የሚገባቸው መሆኑን እንደታመነበት እና

በአጠቃላይ በኦዲት ግኝቱ የተገለጹት ጉዳዮች ራሳችንን ለመፈተሽ የሚረዱ እንደሆነና በኦዲቱ የታዩትን ችግሮች ለማሻሻል የፌዴራል መስሪያ ቤቱ እና የክልል መስሪያ ቤቶችን የሚመለከቱት ተለይተው የማሻሻያ ሃሣብ ቢሰጥ እና በኦዲቱ የተገኙ ግኝቶች ለሚመለከታቸው ክልሎች ቢገለጽ የተሻለ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

# ክፍል አራት

# የማሻሻያ ሐሣቦች

- የግብርና ሚኒስቴር ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መ/ቤቶች ጋር በመተባበር የፀረ-ተባይ ኬሚካል አስመጪ ድርጅቶች፣ የክልል የዞንና የወረዳ ግብርና ጽ/ቤቶች የፀረ-ተባይ ኬሚካል መጋዘኖች በመመሪያው መሠረት ደረጃቸውን ባሟላ መልኩ እንዲገነቡ ክትትል ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡
- የፀረ-ተባይ ኬሚካል ማከማቻ መጋዘኖች ከመገንባታቸው በፊት አስፈላጊውን የስጋት ትንተና በማካሄድ ከሠዎች፣ ከእንስሳትና ከውሀ አካባቢዎች የራቁ መሆናቸውን አስፈላጊው ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የፀረ-ተባይ ኬሚካል የሚያስመጡ ድርጅቶች እና የፀረ-ተባይ ተጠቃሚዎች ለሠራተኞቻቸው አስፈላጊውን የመከላከያ ልብስ፣ ጫማዎች፣ ጓንት እና የመተንፈሻ አካላት መሸፈኛ ቁሳቁሶችን ማሟላታቸውን ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡
- የፀረ-ተባይ ኬሚካል መያዣዎች ፀረ-ተባዩ በሚጓጓዝበት፣ በሚከማችበት፣ ለገበያ በሚቀርብበት፣ በሚከፋፈልበትና ጥቅም ላይ በሚውልበት ጊዜ አደጋ በማያስከትል ሁኔታ ዲዛይን እንዲደረጉ በሀገር ውስጥ ለሚገኘው የአዳሚ ቱሉ የፀረ-ተባይ ፋብሪካና ለአስመጪዎች በጥናት ላይ በመመስረት በማቅረብ ችግሩ ሊፈታ የሚችልበትን መንገድ ማመቻቸት ይጠበቅበታል፡፡
- የግብርና ሚኒስቴር የፀረ-ተባይ ኬሚካል አስመጪዎች ለአበባ እርሻዎች የሚያስመጧቸው ኬሚካሎች የመያዣ ዕቃቸው ላይ መለያው (labeling) በግልጽ በአማርኛና በእንግሊዝኛ እንዲገለጹ እንዲሁም የፀረ-ተባይ ኬሚካሉን የወል መጠሪያ፣ የድብልቅ መጠን፣ የአጠቃቀም መመሪያ፣ ፀረ-ተባዩ ጥቅም ላይ ከዋለ በኋላ አደጋ እንዳያሰከትል መቆየት የሚያስፈልግበት ጊዜ፣ የአለም የጤና ጥበቃ ድርጅት በወሰነው ምደባ መሠረት አደገኛነቱን የሚያስጠነቅቅ የጽሑፍና ስዕላዊ መግለጫ፣ በአደጋ ጊዜ ሊወሰድ የሚገባው የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ አሠጣጥን፣ የተመረተበት ቀን እና የአገልግሎት እድሜውን በግልጽ እንዲለጥፉ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡
- የግብርና ሚኒስቴር ለአበባ እርሻዎች እና ለአትክልትና ፍራፍሬ አገልግሎት የሚውሉ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ተመዝግበው ስራ ላይ እዲውሉ የሚያስችል ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል ፡፡
- የግብርና ሚኒስቴር በተለያዩ የምርምር ማዕከላትና የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በኩል የሚላኩት የፍቱንነት ማረጋገጫ ሙከራዎች ወጥነት እንዲኖራቸዉ የመግባቢያ ሰነድ በማዘጋጀት ከሚመለከታቸዉ ተቋማት ጋር ውይይት በማካሄድ ችግሩን ለመፍታት መንቀሳቀስ ይጠበቅበታል፡፡
- የግብርና ሚኒስቴር ለምዝገባ የሚመጡ የፀረተባይ ኬሚካል ናሙናዎች እና ከተመዘገቡ በኋላ ጥቅም ላይ እንዲውሉ በብዛት (Bulk) በሚገቡበት ወቅት የፍቱንነት ደረጃቸው ተመሣሣይ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥር ተቋቁሞ በነበረው እና አገልግሎት ባቋረጠው በእንስሳት እጽዋት

ጤናና ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት የኬሚስትሪ ላብራቶሪ ይሠራ የነበረው ሥራ ላብራቶሪውን በሚፈለገው ሁኔታ በማደራጀት ሥራውን እንዲጀምር በማድረግ በብዛት (Bulk) የሚገቡት የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች የፍቱንነት ደረጃቸውን የጠበቁ መሆናቸውን ማረጋገጥ እና መከታተል ይጠበቅበታል፡፡

- ጥቅም የሰጡ የፀረ-ተባይ ኬሚካል መያዣዎች ዳግም ለሌላ አገልግሎት ውለው የህብረተሰቡንና አካባቢን ለአደጋ እንዳያጋልጡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የቁጥጥር ሥራ እንዲጠናከር ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡
- የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ተወካይ በፀረ-ተባይ አማካሪ ኮሚቴ ቦርድ ውስጥ በአባልነት በመሳተፉ በተመሣሣይ ሁኔታ የግብር ሚኒስቴር ከፀረ-ተባይ አያያዝና አጠቃቀም አኳያ የሚቀረጹ ብሔራዊ ፖሊሲዎችን፣ ደንቦችን፣ መመሪያዎችን በተመለከተ እንዲሁም ፀረ-ተባይን የሚመለከቱ የዓለም ዓቀፍ ስምምነቶችን ከመተግበር አኳያ ማማከር ይጠበቅበታል፡፡ በመሆኑም የግብር ሚኒስቴር ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ጋር በቅርበት በመነጋገር የመስሪያ ቤቱ ተወካይ በፀረ-ተባይ አማካሪ ቦርዱ ውስጥ የሚሳተፍበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይኖርበታል፡፡
- የግብርና ሚኒስቴር ከፀረ-ተባይ አማካሪ ቦርድ አባላት ጋር ማለትም ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ከአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን፣ ከጥራትና ደረጃዎች ባለስልጣን፣ ከኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣ ከብዝሀ ህይወት ጥበቃ ኢንስቲትዩት፣ ከሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ተወካዮች ጋር ተጠያቂነትን ሊያጠናክር የሚችል እና ለአማካሪ ቦርዱ በአዋጅ የተሠጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችል የመግባቢያ ሰነድ ሊፈራረም ይገባል፡፡
- የግብርና ሚኒስቴር ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የፀረ-ተባይ ኬሚካል በአካባቢና በሕብረተሰቡ ጤና ላይ ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳት ለመቀነስ እና በዓለም አቀፍ ገበያ ተቀባይነት ያለው ምርት ከማቅረብ አንፃር ከፍተኛ ጥቅም ሊያስገኝ የሚችለውን የተቀናጀ የተባይ መከላከያ ስልት (Integrated Pest Management) በሀገሪቱ የሚስፋፋበትን ስልት በመቀየስ የፀረ-ተባይ ኬሚካል አጠቃቀም ሊቀነስ የሚችልበትን መንገድ ሥራ ላይ ማዋል ይጠበቅበታል፡፡
- የግብርና ሚኒስቴር የፀረ-ተባይ ፍላጎት ዳሠሣ ጥናት ከየክልሎች በማሰባሰብ ሀገራዊ የፀረ-ተባይ ፍላጎት ሊያዘጋጅና አስመጪዎችም በፍላጎቱ መሠረት ከውጭ እንዲያስገቡ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ፍላጎትን መሠረት ያደረገ የግብይት ሥርዓት መዘርጋቱ በሀገር ደረጃ ከፍላጎት በላይ ግዥ ቢፈፀም ሊከሰት የሚችለውን አላስፈላጊ ክምችትና በዚሁም ምክንያት የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች አገልግሎት ሳይሰጡ የመጠቀሚያ ጊዜያቸው እንዳያልፍ ለመከላከል ያስችላል፡፡ በሌላ መልኩም አስመጪዎች ከፍላጎት በታች ቢያስገቡ በሀገር ደረጃ ያልተጠበቀ የወረርሽኝ ክስተት ቢከሰት ለመከላከል የሚያስችልን አቅም ስለሚወስን ማኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት ፍላጎትን መሠረት ያደረገ የግብይት ሥርዓትን ማጠናከር ይኖርበታል፡፡
- የግብርና ሚኒስቴር የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች አጠቃላይ መረጃዎችን ለአጠቃቀምና ለውሣኔ በሚያመች መልኩ ማለትም ወደ ኢትዮጵያ የገቡ፣ በኢትዮጵያ የተመረቱና ጥቅም ላይ የዋሉ የፀረ-ተባይ

ዓይነቶችንና መጠናቸውን፣ በመንግስትና በግል ይዞታ ሥር ባሉ መጋዘኖች የሚገኙ ፀረ-ተባዮችን፣ በክምችት ወይም በግብይት ሂደት እያሉ ጥቅም ላይ የማይውሉበት ደረጃ የደረሱ ፀረ-ተባዮችን መረጃ ለመያዝ የሚያስችል የዳታ ቤዝ ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

- የግብርና ሚኒስቴር ተገምግመው የፀደቁ እና የተመዘገቡ ፀረ-ተባዮች እንዲሁም በአገር ውስጥ ጥቅም ላይ እንዳይውሉ እገዳ የተጣለባቸውን ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች አስመልክቶ ለህብረተሰቡ በድረ-ገጽና በህትመት እንዲደርሱና ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚያስችል አሠራር በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን አጠቃቀምና ግብይትን አስመልክቶ በግብርና ሚኒስቴር እና በተለያዩ ባለድርሻ አካላት መካከል የተጠናከረ የመረጃና የግብረ መልስ ሥርዓት ሊኖር ይገባል፡፡
- የግብርና ሚኒስቴር ተመዝግበው ጥቅም ላይ የዋሉ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች የሚጠበቀውን ያክል ውጤት እያስገኙ መሆኑን በትክክል ለማወቅ ውጤታማነታቸውን በየጊዜው መገምገም ይኖርበታል፡፡
- የግብርና ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው የክልል መ/ቤቶች ጋር በመተባበር ለሰብል እና ለእጽዋት የተባይ መከላከያ አገልግሎት ላይ መዋል የማይገባቸውን አደገኛ ኬሚካሎች በህገ-ወጥ መንገድ ጥቅም ላይ እንዳይውሉ አስፈላጊውን ክትትል ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- የፀረ-ተባይ ኬሚካል ንግድ ፈቃድ ያልተሰጣቸው ህገ-ወጥ ግለሰቦች የሚያካሂዱትን የፀረ-ተባይ ኬሚካል ንግድ እንዲቆም ለማስቻል የግብርና ሚኒስቴር ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሊሠራና ክትትል ሊያደረግ ይገባል፡፡
- ግብርና ሚኒስቴር ከክልሎች እና ፀረ-ተባይን ወደ ሀገር ውስጥ ከሚያስገቡ ድርጅቶች ጋር የፀረ-ተባይ ኬሚካል አያያዝና አጠባበቅን በተመለከተ ግንዛቤያቸውን ለማሳደግ የሚያግዙ አመታዊ የውይይት መድረኮችን ማዘጋጀትና በራሪ ጽሑፎችም እንዲደርሳቸው ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡
- የግብርና ሚኒስቴር በፀረ-ተባይ አስመጪዎች መጋዘን እና በክልል፣ በዞን እና በወረዳ ግብርና የፀረ-ተባይ መጋዘኖች ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን በተለየ መጋዘን እንዲያስቀምጡ አስፈላጊውን ግንዛቤ ሊፈጥርና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡
- የግብርና ሚኒስቴር የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች አያያዝና አጠቃቀምን አስመልክቶ ለሚመለከታቸው የክልል እና የዞን የግብርና ባለሙያዎች በቂና ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጫ ድጋፍ በማዘጋጀት በየጊዜው መስጠት ይጠበቅበታል፡፡
- በኦዲት ወቅት በታዩት በደቡብ፣ በአማራ እና በኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮዎች የፀረ-ተባይ ኬሚካል መጋዘኖች ውስጥ ከፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ጋር ተከማችተው የተገኙ ምግብ ነክ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች በህብረተሰቡ ጤና ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርሱ በመሆኑ የግብርና ሚኒስቴር የሚመለከታቸውን የሥራ ኃላፊዎች ችግሩን እንዲያስተካክሉ በማሰባሰብ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡
- የግብርና ሚኒስቴር በኦዲት ወቅት በታዩት በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኘው የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የፀረ-ተባይ መጋዘን፣ በአማራ፣ በኦሮሚያና በደቡብ ክልል ግብርና ቢሮ የፀረ-ተባይ መጋዘኖች ውስጥ

ጊዜ ያለፈባቸው ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች እና በፀረ-ተባይ የተበከሉ ቁሣቁሶች በጥንቃቄ ታሽገው በሰውና በአካባቢ ላይ ጉዳት በማያደርስ መልኩ እንዲጠበቁ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅርበት ሊሠራና ክትትል ሊያደረግ ይገባል፡፡

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እና በኦዲቱ የታዩ ባለድርሻ አካላት ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

አባሪ 1

**የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት**

## <u>የኦዲት መስፈርት መመዘኛዎች</u>

**የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት፣ <u>የግብርና ሚኒስቴር</u>**

| ተ.ቁ | የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች<br>Audit Issues | የኦዲት መስፈርቶች<br>Evaluation Criteria |
|---|---|---|
| 1. | **የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን በመንግስትና በግል ተቋማት ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባትና ጥቅም ላይ ለማዋል በሚ/ር መ/ቤቱ የተዘረጋው የአመዘጋገብ፣ የመረጃ አያያዝና ቁጥጥር ሥርዓት ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ፣** | |
| 1.1 | የመንግስትና የግል ተቋማት የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ለማስገባት የሚኒስቴር መ/ቤቱን የቅድሚያ መስፈርቶች ባሟላ መልኩ ስለመፈቀዳቸው ማረጋገጥ፣ | 1. ፀረ-ተባይን የሚያስመጣው ድርጅት የሚቀጥረው ባለሙያ በሡብል ጥበቃ ቢያንስ 5 ዓመት የስራ ልምድ እና ከድርጅቱ ጋር የ2 ዓመት ህጋዊ ውል ሊኖራቸው ይገባል፡፡ |
| | | 2. የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ማከማቻ መጋዘኖች በሚገነቡበት ወቅት ከጠንካራ ማቴሪያሎች (Galvanized iron, cement stone, brick etc) ሊገነቡ ይገባል፡፡ |
| | | 3. የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ማከማቻ መጋዘኖች ከመስራታቸው በፊት የስጋት ትንተና በማካሄድ ከሠዎች ከእንስሳት እና ውሀ ከሚገኝበት ቦታ ሊርቅ ይገባል፡፡ |
| | | 4. የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን የሚያስመጡ ድርጅቶች ለሠራተኞቻቸው የመከላከያ ልብስ፣ ጫማዎች፣ ጓንት እና የመተንፈሻ አካላት መሸፈኛ ቁሳቁሶችን ማሟላት ይኖርባቸዋል፡፡ |
| | | 5. ማናቸውም ማሸጊያ ፀረ-ተባዩ በሚጓጓዝበት፣ በሚከማችበት፣ ለገበያ በሚቀርብበት፣ በሚከፋፈልበትና ጥቅም ላይ በሚውልበት ጊዜ አደጋ በማያስከትል ሁኔታ ዲዛይን ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | | 6. መንግስታዊና የግል ፀረ-ተባይ አስመጪዎች በአዋጅ ቁጥር 4/1982 የተገለጹትን የኬሚካሉን አጠቃላይ ባህሪ የሚያሳይ መረጃ በመዘርዘር በማሸጊያቸው ላይ መለጠፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡ |
| | | 7. ፀረ-ተባይን በማጠን ንግድ ውስጥ የተሠማሩ ግለሠቦች Gas Mask ከነሙሉ ማቴሪያሎች (canisters) ሊኖራቸው ይገባል፡፡ |
| | | 8. ማንኛውም በፀተ-ተባይ ኬሚካል በማስመጣት ላይ የተሰማራ ነጋዴ ያልተመዘገበ ፀረ-ተባይ ማምረት ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት መሸጥ ወይም መጠቀም አይኖርበትም፡፡ |
| | | 9. የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች የፍቱንነት ሙከራ በሚካሄድበት ወቅት ሪፖርቶች ወጥነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ |
| | | 10. ለምዝገባ የሚመጡ ፀረተባይ ናሙና እና ከተመዘገቡ በኋላ ጥቅም ላይ ሲውሉ ውጤታቸው አንድ ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | | 11. በጤና እና በአካባቢ ላይ ጉዳት እንዳይደርስ በዓለም የጤና |

| ተ.ቁ | የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች<br>Audit Issues | የኦዲት መስፈርቶች<br>Evaluation Criteria |
|---|---|---|
| | | ድርጅት ምደባ መሠረት የተዘረዘሩ 1A እና 1B ፀረ-ተባዮች ጥቅም ላይ ሲውሉ አስፈላጊው የመከላከያ መሣሪያ ሊያሟላ ይገባል፡፡ |
| | | 12. እጅግ አደገኛ የተባሉ የፀረ-ተባይ መያዣዎች ዳግም ጥቅም ላይ እንዳይውሉ ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | | 13. በፀረ-ተባይ አማካሪ ኮሚቴ ውስጥ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ተሣተፊ ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | | 14. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባለው የፀረ-ተባይ አማካሪ ቦርድ ከቦርዱ አባላት ጋር የመግባቢያ ሰነድ ሊኖር ይገባል፡፡ |
| | | 15. የተቀናጀ የፀረ-ተባይ መከላከያ ስልት (IPM) በማስፋፋት የፀረ-ተባይ አጠቃቀምን ሊቀነስ ይገባል፡፡ |
| 1.2 | የፀረ-ተባይ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት ውጤታማነትን መፈተሽ፣ | 16. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ-ተባይ ፍላጐት ዳሠሣ ጥናት ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | | 17. የፀረ-ተባይ ፍላጐት ዳሠሣ ጥናት በሚካሄድበት ወቅት የአገሪቷን ፍላጐት፣ የህብረተሰቡን አቅም፣ የትምህርት ደረጃ እና የአየር ሁኔታ መሠረት ያደረገ ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | | 18. ሚ/ር መ/ቤቱ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን የመስክና የላብራቶሪ ውጤቶችን በመተንተን ለውሣኔ ሃሣብ የሚረዳ መረጃ መያዝ ይኖርበታል፡፡ |
| | | 19. መ/ቤቱ እራሱ መግባት ያለባቸውን የፀረ-ተባዮች ዝርዝር ሊይዝ ይገባል፡፡ |
| | | 20. እጅግ አደገኛ፣ አደገኛ፣ መካከለኛ እና ዝቅተኛ አደጋ ተብለው በWHO classification ደረጃ የተሠጣቸው ፀረ-ተባዮች በየምድባቸው ተለይተው ሊመዘገቡ ይገባል፡፡ |
| | | 21. ጥቅም ላይ የሚውሉ ፀረ-ተባዮች ዓይነታቸውና ብዛታቸው በሚታወቅበት መልኩ በdata base system በታገዘበት ሁኔታ በዝርዝር ሊቀመጥ ይገባል፡፡ |
| | | 22. በፀረ-ተባይ ንግድ የተሠማራ ግለሠብ ወይም ድርጅት እንዲሁም ክልሎች ያስገቡትን፣ ያከማቹትን እና የሸጡትን በሚያሣይ መልኩ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሪፖርት የሚያደረጉበትን ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ |
| | | 23. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አገራዊ የፀረ-ተባይ አጠቃቀም መረጃዎችን በማሠባሠብ የስጋት ትንተና እና የስጋት ማስወገጃ (Risk analysis and management) ሊሠራ ይገባል፡፡ |
| | | 24. ተገምግመው የፀደቁ ፀረ-ተባዮች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ለፀረ-ተባዮች የምዝገባ ሰርተፍኬት መስጠት፣ በድረ-ገጽ ማሠራጨትና በዓመቱ የተመዘገቡ ፀረ-ተባዮችን ዝርዝር በህትመት በማዘጋጀት ለተጠቃሚዎች እንዲደርሱና ጥቅም ላይ እንዲውሉ የማሣወቅ ሥራ ሊያከናውን ሚኒስቴር መ/ቤቱ ይገባል፡፡ |
| | | 25. በፀረ-ተባይ ኬሚካሎች አገባብ፣ አጠቃቀምና አወጋገድ ላይ የሚታዩ የአሠራር ግድፈቶች የሚገለጹበት የግብረ መልስ ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ |
| | | 26. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን በተመለከተ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት፣ ከክልል ግብርና ቢሮዎች፣ |

| ተ.ቁ | የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች<br>Audit Issues | የኦዲት መስፈርቶች<br>Evaluation Criteria |
|---|---|---|
| | | ግብረሰናይ ድርጅቶች ጋር ያለው የመረጃ ልውውጥ መደበኛ በሆነ የሪፖርቲንግ ስርዓት መሠረት መሆን አለበት፡፡ |
| 1.3 | ተመዝግቦ ጥቅም ላይ የሚውሉ ፀረ-ተባዮችን በሚመለከት የተዘረጋው የቁጥጥር ሥርዓት ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ፣ | 27. ተመዝግበው ጥቅም ላይ የዋሉ ፀረ-ተባዮች በዓመት አንድ ጊዜ ውጤታማነታቸው ሊገመገም ይገባል፡፡ |
| | | 28. ኢንስፔክተሩ ፀረ-ተባዩ ባለበት ሥፍራ ተገኝቶ አስፈላጊው መረጃ ወይም ቀድሞ የተሠጠ የማስገቢያ ፈቃድ ቢል ኦፍ ሎዲንግ ፀረ-ተባዩ ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ የተጠየቀው ስለመሆኑ፣ በህጉ መሠረት የመለያ ምልክት መኖሩንና መለያ ምልክቱ ላይ አስፈላጊው መረጃ መኖሩ፣ ከተፈቀደበት አገር የመጣ መሆኑንና በመመሪያው መሠረት መታሸጉንግ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| | | 29. ባለሀብቶች በልዩ ፍቃድ ከውጭ አገር አስገብተው በራሣቸው ማሣ ላይ ጥቅም ላይ የሚውሉ ፀረ-ተባዮችን ሚኒስቴር መ/ቤቱ ክትትልና ግምገማ እያደረገ ብቃታቸዉን በማሳ ላይ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| | | 30. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በተለያዩ ህገ-ወጥ መንገዶች ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ፀረ-ተባዮችን በመከታተል ጥቅም ላይ እንዳይውሉ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ |
| | | 31. ፀረ-ተባዮች ከውጭ ወደ አገር ውሰጥ ሲገቡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ጋር በመቀናጀት የፀረ-ተባይ አስገቢ ባለሀብቱ በተፈለገው ጊዜ፣ የተፈቀደለትን መጠን ማስገባቱን ማረጋገጥ አለበት፡፡ |
| 2 | **ፀረ-ተባይ በሠው ጤና እና በአካባቢ ላይ ጉዳት በማያደርስ መልኩ መጠበቁን፣ መጓጓዙን እና ጥቅም ላይ መዋሉን የተዘረጋውን ሥርዓት ውጤታማነት ማረጋገጥ፣** | |
| 2.1 | ፀረ-ተባይ በሠው ጤና እና በአካባቢ ላይ ጉዳት በማያደርስ መልኩ መጠበቁን ማረጋገጥ፣ | |
| | | 32. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ-ተባይ ንግድ የተሠማራ ግለሠብ ወይም ድርጅት ያስገባውን፣ ያከማቸውን እና የሸጠውን በሚያሣይ መልኩ መዝገብ እንዲያደራጁ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | | 33. ከክልሎች እና ፀረ-ተባይን ወደ ሀገር ውሰጥ ከሚያስገቡ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ድርጅቶ በፀረ-ተባይ አያያዝ ዙሪያ የሚወያይበት መድረክ ሊኖር ይገባል፡፡ |
| | | 34. ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ እና ጊዜያቸው ያለፈባቸው ፀረ-ተባዮች በተለያየ ቦታ መከማቸት እንዳለባቸው ፀረ-ተባይን ወደ ሀገር ውስጥ ለሚያስገቡ እና ለተጠቃሚዎች ግንዛቤ ሊሠጥ እና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | | 35. በክልሎች ላይ ያሉ የግብርና ባለሙያዎች በፀረ-ተባይ ዙሪያ ያላቸውን ግንዛቤ ለማሳደግ እና ለፀረ-ተባይ ተጠቃሚ አርሶ አደሮች እንዴት መጠበቅ እንዳለበት የግንዛቤ ማስጨበጫ እንዲሰጡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአቅም ማጐልበቻ ድጋፍ (Capacity building) ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | | 36. ፀረ-ተባይን ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገቡ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች ፀረ-ተባይን የሚያከማቹበት መጋዘን በFAO መመሪያ መሠረት መጠበቃቸውን መከታተል አለበት፡፡ ይገባል፡፡ |
| | | 37. የመስክ ሥራ ቁጥጥር ተደርጐ በቀረበ ሪፖርት ላይ የማስተካከያ |

| ተ.ቁ | የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች<br>**Audit Issues** | የኦዲት መስፈርቶች<br>**Evaluation Criteria** |
|---|---|---|
| | | እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ |
| 2.2 | የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ከቦታ ቦታ ሲጓጓዙ የሚኒስቴር መ/ቤቱን መስፈርት ባሟላ መልኩ መሆኑን ማረጋገጥ፣ | |
| | | 38. መንግስታዊም ሆነ በፀረ-ተባይ ንግድ ላይ የተሠማሩ ባለሀብቶች ፀረ-ተባይን በሚያጓጉዝበት ወቅት በሠው ጤና እና በአካባቢ ላይ ጉዳት በማያደርስ መልኩ እንዲጓጓዝ የቁጥጥር ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ |
| 2.3 | ፀረ-ተባይ ጥቅም ላይ በሚውልበት ወቅት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያለው የቁጥጥር ሥርዓት በአጥጋቢ ሁኔታ መተግበሩን ማረጋገጥ፣ | |
| | | 39. ፀረ-ተባይን ወደ አገር ውስጥ ለሚያስገቡ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች ቀድመው ወደ አገር ውስጥ የገቡ ፀረ-ተባዮች ቀድመው ጥቅም ላይ ማዋላቸውን (FIFO) ለማረጋገጥ የተዘረጋው የቁጥጥር ሥርዓት ውጤታማ ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | | 40. እጅግ አደገኛ የሆኑ ፀረ-ተባዮች በባለሙያ ብቻ ጥቅም ላይ እንዲውሉ የተዘረጋው የቁጥጥር ሥርዓት ውጤታማ ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | | 41. አርሶ አደሩም ሆነ ሌሎች የፀረ-ተባይ ተጠቃሚዎች በሠው ጤና እና በአካባቢ ላይ ጉዳት በማያደርስ መልኩ እንዲጠቀሙ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | | 42. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፀረ-ተባይን በብዛት የሚጠቀሙና የአቅም ችግር ያለባቸውን ክልሎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች አጥንቶ የአቅም ግንባታ ሥራ ሊሠራ ይገባዋል፡፡ |
| | | 43. እጅግ አደገኛ የተባሉ ፀረ-ተባዮች የሚጠቀሙ የእርሻ ተቋማት በሚጠቀሙበት ወቅት አስፈላጊው የመከላከያ እና የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ መስጫ ቁሳቁሶችን ሊሟሉ ይገባል፡፡ |
| 3 | **ፀረ-ተባዮች በወቅቱ ጥቅም ላይ እንዲውሉና እንዳይበላሹ አስፈላጊው ቁጥጥር መደረጉንና የተበላሹ ፀረ-ተባዮች ባግባቡ መከማቸታቸውንና መወገዳቸውን ማጣራት፣** | |
| 3.1 | ፀረ-ተባዮች በወቅቱ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ | 44. በግዥ ወይም በእርዳታ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲይገቡ የሚፈቀዱ ፀረ-ተባዮች ከተመረተበት ጊዜ ከስድስት ወር መብለጥ የለበትም፡፡ |
| | | 45. በግዥ አልያም በእርዳታ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ፀረ-ተባዮች የፀረ ተባዩ የአገልግሎት ዘመን ከማለቁ በፊት ጥቅም ላይ ሊውሉ ይገባል፡፡ |
| | | 46. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተለያዩ አካላት ወደ ሀገር ውስጥ ያስገቡአቸውና ሊጠቀሙባቸው ያልቻሉትን ፀረ-ተባዮች የአገልግሎት ዘመናቸው ከማለቁ በፊት ሌሎች እንዲጠቀሙበት የማግባባትና የማስተባበር ሥራዎችን ሊሰራ ይገባዋል፡፡ |
| | | 47. 3.1.5 የእንስሳትና እጽዋት ጤናና ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ወደ ሀገር ውስጥ የገቡና ጥቅም እየሰጡ ያሉ ፀረ-ተባዮችና ያጋጠሙ ችግሮችን ባካተተ መልኩ የሩብ፣ የግማሽና አመታዊ ሪፖርት ውስጥ እያካተተ ለግብርና ልማት ዘርፍ ሪፖርት ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| 3.2 | ጊዜያቸው ያለፈባቸው ፀረ-ተባዮች በተቀመጠው ደረጃ መሠረት መከማቸታቸውንና መወገዳቸውን ማጣራት፣ | |

| ተ.ቁ | የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች<br>Audit Issues | የኦዲት መስፈርቶች<br>Evaluation Criteria |
|---|---|---|
| | | 48. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሀገሪቷ ውሰጥ በወቅቱ ጥቅም ሊሰጡ ያልቻሉ ፀረ-ተባዮች፣ የተበከሉ የፀረ-ተባይ መያዣዎች፣ የተበከሉ አፈሮች በአይነትና በመጠን እንዲሁም በቦታ እየተዘረዘሩ ፀረ-ተባይን ከሚጠቀሙ አካላት ጋር የተጠናከረ የመረጃ ልውውጥ ሊኖረው ይገባል፡፡ |
| | | 49. ጊዜ ያለፈባቸውም ጥቅም ሊሰጡ ያልቻሉ ፀረ-ተባዮች በጥንቃቄ ታሽገው ለሰውና ለአካባቢ ጉዳት በማያደርስ መልኩ ሊከማቹና ሊጠበቁ ይገባል፡፡ |
| | | 50. ጊዜ ያለፈባቸው ፀረ-ተባዮች ሲወገዱ ከጉዳት መጠናቸው አንፃር መጀመሪያ እጅግ ጎጂ የተባሉትን በማስቀደም መሆን ይገባዋል፡፡ |
| | | 51. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጊዜያቸው ያለፈባቸውን ፀረ-ተባዮች በማሰባሰብ፣ በማከማቸትና በማጓጓዝ ሥራ ውስጥ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በማሣተፍ በቅንጅት ሊሠራ ይገባል፡፡ |
| | | 52. በተለያዩ ጊዜያቶች ጊዜያቸው ያለፈባቸው ፀረ-ተባዮች ለማስወገድ የተቋቋሙ ኘሮጀክቶች የተመደበላቸውን በጀት በብቃት ሊጠቀሙ ይገባል፡፡ |